Habtamu Hailemeskel- Attorney & Consultant

ረቂቅ

የኢትዮጵያ ንግድ ፖሊሲ

ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

ሚያዚያ 2015

አዲስ አበባ

ማውጫ

1 መግቢያ 2
2 ራዕይ 3
3 የፖሊሲው አስፈላጊነት 3
4 የፖሊሲ አላማ 6
5 የፖሊሲ ጉዳዮች 7
5.1 የሀገር ውስጥ ንግድ እና ስርጭት 8
5.2 ለንግድ ስርአቱ ምቹ የማክሮ ኢኮኖሚ ካባቢ 10
5.3 ኢንቨስትመንት እና ንግድ 11
5.4 የንግድ ወጪን መቀነስ እና አለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ 14
5.5 የገበያ ተደራሽነትን ማስፋት 16
5.6 የወጪ ንግድ ብዝሀነት 19
5.7 በአለም አቀፍ እሴት ሰንሰለት ዉስጥ መሳተፍ 20
5.8 ዲጂታል ንግድ 22
5.9 የሸማቾች ጥበቃ እና ፍትሃዊ ንግድ 23
5.10 ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች 25
5.10.1 ስርዓተ ጾታ 25
5.10.2 የአየር ንብረት ለውጥ 26
5.10.3 ስራና ሰራተኛ 27
5.10.4 የአካል ጉዳተኛ አካታችነት 27
5.10.5 ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች 28
6 የፖሊሲው ቁልፍ ውጤቶች 29
7 ፖሊሲ የማውጣት ስልጣን 30
8 የፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስልት 31
8.1 ፈፃሚ ተቋማት 32
8.2 የህግ ማእቀፍ 33
8.3 የልማት ፕሮግራሞች 34
8.4 የፖሊሲ ክትትልና ግምገማ 38
9 ተያያዥ ፖሊሲዎች 42
10 የፖሊሲው ስርጭት 43
11 ፖሊሲው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ 43
12 የቃላት ፍች 44

1 መግቢያ

የንግድ ስራ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ቀደምት እና የኢኮኖሚ ማዕከል ሆኖ የቆየ ቢሆንም እስከ አሁን የሀገሪቱን የሀገር ውስጥና አለም አቀፍ ንግድ ስርዓትን በአግባቡ የሚመራ አጠቃላይና ወጥ የሆነ የንግድ ፖሊሲ አልነበረም። በመሆኑም በፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አፈፃጸም እና በንግድ ዘርፉ ላይ ያሉ የንግድ እድሎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ስታንዳርዶች በተመለከተ የአሰራር ወጥነት ችግሮች ይስተዋላል። በዚህ ምክንያት የሚፈፀሙ ህገወጥ የንግድ ተግባራት፣ የተለያዩ የንግድ ዘርፎችን የሚመሩ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ የሚደረጉ ያልተጠበቁ ተደጋጋሚ ለውጦች፣ ለሚያጋጥሙ የንግድ ሎጅስቲክ ችግሮች መፍትሄ የሚሰጡ በቂ የአሰራር ስርዓቶች አለመቀረፅ እንዲሁም በየጊዜው በሚፈረሙና እያደጉ ባሉ የሀገራት የንግድ ስምምነቶች ላይ መተማመን መፍጠር አለመቻል ይታያል። በተጨማሪም ተገማች ያልሆነው ሀገራዊ የንግድ አሰራር ሁኔታ በንግድ ከባቢው እና በኢንቨስትመንት ልማት ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል። የንግድ ፖሊሲ እስከ አሁን ያልተቀረጸ ቢሆንም በተለያዩ ጊዜያት በተዘጋጁ የኢንዱስትሪና የሌሎች ዘርፍ ፖሊሲዎች፣ በንግድ ህግ እንዲሁም በተለያዩ ተያያዥ የፖሊሲ ሰነዶች ላይ በመመስረት የንግድ ስርዓቱ ሲመራ ቆይቷል። ለዚህም እንደ ምሳሌ የንግድና ኢንዱስትሪ ዘርፍ የፖሊሲ አቅጣጫዎች እና በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ I እና II ላይ በተወሰነ ደረጃ መጠቀሱ ነው።

ምንም እንኳን ይህ እስካሁን ድረስ የንግድ ፖሊሲ ባይኖርም ኢትዮጵያ በሁለትዮሽ፣ በቀጣናዊ፣ በአህጉራዊ እና አለም አቀፍ የንግድ ስምምነቶች ለረጅም አመታት ስትሳተፍ ቆይታለች። ከእነዚህም ግንኙነቶች መካከል የምስራቅ አፍሪካ የልማትበይነ መንግስታት (IGAD)፣ የምስራቅ እና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ (COMESA)፣ የአፍሪካ እና አረብ እንዲሁም ፓስፊክ ሀገሮች ህብረት (ACP)፣ የሶስትዮሽ ቀጣና ድርጅቶች (COMESA,SADC and EAC)፣ የሶስትዮሽ ነጻ የንግድ ዞን (Tripartate Free Trade Area)፣ የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጣና (AfCFTA)፣ እንዲሁም የአለም ንግድ ድርጅት (WTO) ይጠቀሳሉ። በተጨማሪም ከአህጉራዊ ግንኙነት በተሻገረ ከአውሮፓ ህብረት ጋር የምታደርገው የንግድ ልውውጥ ከጦር መሳሪያዎች በስተቀር ማንኛውም (EBA) በሚል የንግድ ስምምነት እና በአሁኑ ጊዜ ከአውሮፓ ህብረት ጋር የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት ለመፈፀም በመደራደር ላይ ትገኛለች።

የኢትዮጵያ የንግድ ፖሊሲ የሀገራቱን የንግድ ስርዓት የሚመራ እንደመሆኑ መጠን ቀጣይ የንግድ ድርድሮችን፣ ስምምነቶችን ፣ ውህደትን፣ አለም አቀፋዊ ተሞክሮዎችን እና የንግድ ሰንሰለት ነባራዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ያስገባ ነው። የንግድ ፖሊሲው መነሻ ሀገራችን ቅድሚያ ትኩረት በምትሰጥባቸው እና የዓለም አቀፍ ንግድ ትኩረት የሆኑትን ምርትና አገልግሎቶች እንዲሁም የአግሮ ኢንዱስትሪ ዘርፎች እና በአሁኑ ጊዜ በአለም አቀፍ ደረጃ ወሳኝ በሆነው የንግድ ሰንሰለቶች ላይ ያተኮረ ነውል።

ፖሊሲው የንግድን ሁሉ አቀፍ ሴክተራል ባህሪ በመረዳት የፖሊሲ ቅንጅትንና ወጥነትን ለማረጋገጥ ቀረጻው ከሌሎች አገራዊና ዘርፍ ፖሊሲዎች ጋር እንዲተሳሰር ተደርጓል። ስለዚህ በዚህ ሰነድ ውስጥ የተዘረዘሩትን የፖሊሲ እርምጃዎች በተሳካ ሁኔታ ለመተግበር የሚኒስተር መሰሪያ ቤቶች ትብብር ቁልፍ ይሆናል። የኢትዮጵያ ንግድ ፖሊሲ ሰነድ በዋናነት የፖሊሲ መግለጫዎችን፣ የፖሊሲ ዓላማዎችን፣ የፖሊሲ ጉዳዮችንና ዝርዝር አቅጣጫዎችን እና የፖሊሲ ትግበራ ስልቶችን ይዟል።

2 ራዕይ

ቀልጣፋ የአገር ውስጥ ገበያ ስርአት እና በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ኢኮኖሚ ተገንብቶ ማየት።

3 የፖሊሲው አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ የልማት እቅድ ዘላቂ፣ ፈጣን፣ ሰፊ መሰረት ያለውና አካታች የሆነ ከኢኮኖሚ እድገቱ ጋር አብሮ የሚሄድ ንግድን በማስፋፋት እና የወጪ ምርት አይነቶችና የመዳረሻ ገበያዎችን በማሳደግ የአፍሪካ የብልፅግና ሞዴል መሆን ነው። ከለውጡ ማግስት ጀምሮ መንግስት በኢኮኖሚ እድገት ላይ የያዛቸው እቅዶች መሰረት የሚያደርጉት ባለፉት አመታት የታዩትን ተግዳሮቶች በማጤን እና የኢኮኖሚውን ልዩ ሁኔታዎች እና በቀጣይ በኢኮኖሚ ዕድገቱ ልዩ ባህርይ ያላቸውን እንደምታዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው። የንግድ ስርዓታችን ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ምርታማነትን በማሳደግ፣ የማምረት ብቃትን ፣ አቅምን እና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ እና የሀገሪቱን የወጪ ንግድ ዘርፍ በማላቅ ነው። የንግድ ፖሊሲው የሚመሰረተው ጠንካራ የሆነ የንግድ ዘርፍን በመፍጠር ፣ ፍትሐዊ የሆነ የውድድር አውድ እንዲኖር በማድረግ፣ በተመረጡ ዘርፎች የመንግስት ጣልቃ የመግባት ጠቀሜታን ቸል ባለማለት እና ክፍተቶችን ለመሙላት የሚደረገውን ጥረት በማጠናከር ነው። የኢትዮጵያ

ኢኮኖሚ በዋነኝነት በግብርና ላይ የተመሰረተ ሲሆን ከዚሁ ዘረፍ የሚገኘው ወጭ ምንዛሬ ገቢም ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡ በመሆኑም ኢኮኖሚውን ለአለም አቀፍ የምርቶች ዋጋ መዋዠቅና ተለዋዋጭ ለሆነው ለአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖ አጋልጦታል፡፡ ስለሆነም መንግስት በዚህ የንግድ ፖሊሲ ማሻሻያ አጀንዳ በመመስረት ተግዳሮቶችን ለመፍታት በንግድ ፖሊሲው የሚወሰዱ እርምጃዎችን ከፊሲካል፣ ሞኒተሪ እና የኢንዱስትሪ ፖሊሲዎች ጋር በማጣጣም ለመስራት አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡

ሀገራችን የንግድ ግንኙነቷን ለማስፋት ከበርካታ መንግስታት የሁለትዮሽ ፣ቀጣናዊ እና አህጉራዊ ስምምነቶች አድርጋለች፡፡ ሆኖም ወጥ የሆነ የንግድ ፖሊሲ ሰነድ ባለመኖሩ መንግስትና የንግዱ ህብረተሰብ ስለ ንግድ ህጎች፣ደንቦች እንዲሁም ስለ ዓለም አቀፍ የንግድ እድሎች ያላቸው ግንዛቤ እና አመለካከት አናሳ እንዲሆን መንገድ ፈጥሯል፡፡ ስለዚህ የንግድ ፖሊሲው የሀገሪቱን የንግድ ዘርፍ አሰራር፣ ድርድሮችን፣ ስምምነቶችን እንዲሁም ውህደትን የሚመራ በመሆኑ የንግድ ፖሊሲው በሚኒስቴር መ/ቤቶች ውይይት፣ በባለድርሻ አካላት ምክክር እና የግል ዘርፉ እና የሲቪል ማህበረሰቡ ጋር በሚደረግ የጋራ መድረክ ዳብሮ ለሁሉም ዜጎች በፍትሃዊነት የስራ እድል መፍጠር እንዲችል፤ ሴቶችና ወጣቶችን ወደ ብልጽግና መንገድ እንዲያመራ እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ጠንካራ ኢኮኖሚን ለመገንባት የታቀዱትን ግቦች እንዲሳኩ ያግዛል፡፡

የሀገሪቱን የንግድ ስርዓት፣ ድርድሮችን፣ ስምምነቶችን እንዲሁም ውህደትን የሚመራው የኢትዮጵያ ንግድ ፖሊሲ ዘላቂና ፍትሃዊ እንዲሆን አለም አቀፍ የእሴት ሰንሰለት (global value chain) ሂደቶችን ከግንዛቤ ያስገባ መሆን ያስፈልገዋል፡፡ የንግድ ጽንሰ ሀሳብ እስከ አለም አቀፍ የምርት እሴት ሰንሰለት መሳተፍ ድረስ የዘመነ ሲሆን ኢትዮጵያ ምንም እንኳን የጎላ ተሳትፎ ባይኖራትም መንግስት በአግሮ ኢንዱስትሪ፣ በጨርቃ ጨርቅ እና በአልባሳት ዘርፎች ከሚያደርጋቸው ተሳትፎዎች አኳያ በዚህ እሴት ሰንሰለት ውስጥ ለመሳተፍ እድል እንዲኖራ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም የንግድ ፖሊሲው የሀገሪቱ የንግድ ተዋናዮችና አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች በአለም አቀፉ የምርት እሴት ሰንሰለት ውስጥ እንዲሳተፉ እንዲሁም በአህጉራዊ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ በአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጣና ውስጥ ከቀጣናው አጋሮች ጋር ንግድን ለማሳለጥ የገቢ ንግድ ታሪፎችን በማንሳት ተሳትፎ ለማድረግ የሚያስችል አይነተኛ መፍትሄ ሆኖ ያገለግላል፡፡ የንግድ ልውውጡ ከታሪፍ ውጪ የሆኑ መሰናክሎችን ለምሳሌ የጉምሩክ ሂደት መዘግየትን፣ ከመነሻው እስከ መድረሻ ያሉ የትራንስፖርትና ሎጀስቲክ

አቅርቦቶች እጥረትን እንዲሁም ተደጋጋሚ የሆኑ የወረቀት ስራዎችን ማስወገድን ይፈልጋል። ስለዚህ ይህ የንግድ ፖሊሲ በበርካታ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ቅንጅት እንዲፈጠር፣ ሰራተኞች ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ፣ የጉምሩክ ስርዓቱ ዲጂታል እንዲሆን፣ የገበያ መሰረተ ልማቶችን ለመገንባት፣ የድንበር ንግድ እንቅስቃሴ መዘግየትን ለመቅረፍ ያግዛል። በእርግጥ ንግድ ባለፉት ሀገራዊ የእድገት ሂደቶች ላይ ጉልህ ድርሻ ቢኖረውም ንግድን በማፋጠን እና ንግድ መር እድገት ለማድረግ ወጥ የንግድ ፖሊሲ ሰነድ ሲዘጋጅ ይህ የመጀመሪያ ነው። ይህ የንግድ ፖሊሲ የኢትዮጵያን የንግድ ስርዓት የሚመራ፣ ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲሁም የኢኮኖሚውን ሂደት መልክ ብዙ በማድረግ አስተማማኝ እና ተጨባጭ የሆነ ልማት ለማምጣት የሚያገለግል ዋነኛ መሳሪያ ነው።

የንግድ ስርዓቱ በበርካታ ፈተናዎች ውስጥ ያለ ሲሆን ዋጋ አሳንሰው የሚልኩ እና ዋጋ አሳንሰው ወይም አስበልጠው የሚያስመጡ፣የጥራት ደረጃቸውን ያልጠበቁ ምርቶችን የሚያመርቱ እና የሚያስመጡ እንዳሉ ሁሉ የሎጂስቲክስ አቅርቦቱ አለመጣጣም እና በዘርፉ ያሉ ህጎችና አሰራሮች በየጊዜው መለዋወጥ ተግዳሮት ናቸው። ስለዚህ የንግድ ፖሊሲው የሀገሪቱን የእሴት ሰንሰለት ትስስር ውስጥ በማስገባት የኤክስፖርት ገቢን ለመጨመር፣ የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ለመሳብ እንዲሁም ና በቴክኖሎጂ የተደገፈ አሰራር ለመዘርጋት እና የእውቀት ሽግግር ለመፍጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል። ይህም ጠንካራ፣ ዘርፈ ብዙ፣ አስተማማኝ እና በውድድር ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ ለመፍጠር እና በአፍሪካ የኢንቨስትመንት ማዕከል ለመሆን አይነተኛ መሳሪያ ነው። በተጨማሪም የምርት ልውውጥና የግብዓት አቅርቦት ወጪዎችን በመቀነስ እንዲሁም በኢንቨስትመንት የሚፈሰውን መዋዕለ ንዋይና እሴት የተጨመረባቸው ምርቶችን በማሳደግ ስትራቴጂያዊ ጥቅም ባላቸው የግብርና ምርቶች ንግድና በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ስራዎች ላይ ለመሳተፍ የሚያስችል ሀገራዊ ፣ አህጉራዊ እና አለም አቀፍ የእሴት ሰንሰለት ተወዳዳሪነትን ለመፍጠር ያግዛል። በተመሳሳይ በባለድርሻ አካላት እንዲሁም በኢንዱስትሪው እና በኢንቨስተሮች መካከል ያለውን ትስስር በማጠናከር ልማትን ለማምጣት እና ድህነትን ለመቀነስ የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ ይረዳል።

የንግድ ፖሊሲው ሀገራዊ ተወዳዳሪነትን የማሳደግ፣ ወጪ ንግድን የማስፋፋት እና የወጪ ምርቶችን በዓይነት፣ በመጠን እና በመዳረሻ ገበያ የማስፋት፣ ፈጠራንና ግልፅነትን የማበረታታት እና የንግድ እድሎችን ለማስፋት እንዲሁም በሀገር ውስጥ ንግድ፣ በጠረፍ ንግድ ላይ እና በመዳረሻ ገበያዎች ያሉትን መሰናክሎችን በመቅረፍ ረገድ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን

ጉዳዮች የያዘ ነው። እንዲሁም ፖሊሲው በሰራተኛው እውቀትና ክህሎት ለማሻሻል እና የተቀመጡ የአከባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ግቦችን እንዲሁም ለሴቶችና ወጣቶች በሚፈጠሩ የስራ እድሎች ላይ ያለመ በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ሀብት ለመፍጠር ያግዛል።

4 የፖሊሲ አላማ

የንግድ ፖሊሲው ዋና ዓላማ ፍትሃዊ ፣ ግልፅ ፣አካታች እና በውድድር ላይ የተመሰረተ የሀገር ውስጥ ንግድ እና ተወዳዳሪ የወጪ ንግድ ስርዓት በመገንባት በሀገር የኢኮኖሚ ግንባታ፣ በድህነት ቅነሳ እና ዘላቂ ልማት ለማምጣት ጉልህ ሚና እንዲጫወት ማስቻል ነው።

ዝርዝር ዓላማዎች ፡-

1. የግሉን ዘርፍ የማምረት አቅም፣ ምርታማነት እና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ።
2. ኢንተርፕራይዞችን በአህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ እሴት ሰንሰለቶች (GVC) ውስጥ ትስስራቸውን ማቀናጀት።
3. በሁለትዮሽ፣ በአህጉራዊ አጋርነት እና በባለብዙ ወገን የንግድ ስምምነቶች ለኢትዮጵያ ምርትና አገልግሎት የገበያ መዳረሻ እድል መፍጠር።
4. የንግድ ድርጅቶች ዕቃና አገልግሎት ዲጂታል ንግድ ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ። የዲጂታል ንግድ የኢትዮጵያ ኩባንያዎች ምርቶች (ዕቃዎች) እና አገልግሎቶች በዲጂታል ተያያዥነት ላላቸው ዓለም አቀፍ የገበያ ቦታዎች ቀርበው ቀላል፣ በተመጣጣኝ ዋጋ እና ይበልጥ ግልጽ በሆነ ውድድር እንዲሸጡ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
5. የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ጨምሮ ለውጭ ገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ ምርቶች እና አገልግሎቶች ለማምረትና ለማቅረብ የሚያስችል ምቹ ካባቢ መፍጠር እና ከሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ጋር በእውቀት ላይ የተመሰረተ ምቹ ኢኮኖሚ እና ከባቢ በመፍጠር ተሳትፎ እንዲጨምር ማድረግ፣
6. የሻማቾች ጥበቃ እና ፍትሃዊ የገበያ ውድድርን ለማስፈን፣
7. ለንግድ ስርአቱ አስቻይ የሆነ የተረጋጋ የማክሮ- ኢኮኖሚ ካባቢ ለመፍጠር ነው።

5 የፖሊሲ ጉዳዮች

ለሁለት አስርት ዓመታት ያህል የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት ያስመዘገበው በዋነኛነት ከፍተኛ የመንግስት ወጪ በሃይል፣ በትራንስፖርት፣ በኮሙዩኒኬሽን እና በኢንዱስትሪላይዜሽን መሰረተ ልማት ኢንቨስትመንት የተመሰረተ ነው። ይሁን እንጂ ኢኮኖሚው በተመሳሳይ ጊዜ የዕዳ ጫና እና ቀጣይነት ያለው የማክሮ ኢኮኖሚ ሚዛን ጉድለት፣ የንግድ ሚዛን አለመጣጣም፣ የበጀት ጉድለት፣ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት እና የውጭ ብድር ተጋላጭነት ችግሮች አጋጥመዋል። በዚህም መሰረት ከ2010 አጋማሽ ጀምሮ መንግስት እነዚህን መዋቅራዊ ችግሮች ለመፍታት ሁሉን አቀፍና ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ማለትም ማክሮ ኢኮኖሚ እና የፋይናንስ ዘርፍ ማሻሻያ፣ የተቋማት መዋቅራዊ ማሻሻያ፣ የህግ ማዕቀፎች እና የአስተዳደራር ዘርፍ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ተደርጓል።

የኢትዮጵያ መንግስት የ10 አመት የልማት እቅድ (2013-2022) በግልፅ እንዳስቀመጠው በ2022 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት መካከል ለመቀላቀል እና ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ ህዝቦችን ምጣኔ በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 19 በመቶ ወደ 7 በመቶ ለማውረድ ያለመ ነው። ዋነኛ የብልጽግና ጉዞ እቅድ ምሰሶዎች ተብለው የተቀመጡት ጥራት ያለው ዕድገት ማረጋገጥ፣ ምርታማነት እና ተወዳዳሪነትን ማሻሻል፣ ተቋማዊ ለውጥ ማድረግ፣ የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን የመሪነት ሚና ማረጋገጥ፣ የሴቶችና ህጻናት ፍትሃዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት ነቸው።

ልማትን መነሻ ያደረገው ሁሉን አቀፍ የንግድ ፖሊሲ ምርታማነት፣ ተወዳዳሪነት እና ቅልጥፍናን በማጎልበት፣ የማምረት አቅም እና ኤክስፖርትን በማሳደግ መንግስት እያካሄደ ያለውን የኢኮኖሚ ማሻሻያና የልማት ግቦችን ለማሳካት ዓይነተኛ ሚና ይጫወታል። መንግስት ያስቀመጠውን የልማት ግብ ለማሳካት ንግድ ወሳኝ ሚናውን መጫወት እንዲችል የ10 አመት የወጪ ንግድ ልማትና ፕሮሞሽን ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል።

የዓለም አቀፍ የንግድ ስምምነቶች እና የተለያዩ ሀገራት የንግድ ፖሊሲዎች በዋናነት ትኩረት የሚያደረጉት የታሪፍ ቅናሳ ላይ ብቻ ሳይሆን በርካታ ሴክተሮችና የኢኮኖሚ ዘርፎችን ያካተቱ ናቸው። ስለሆነም የንግድ ፖሊሲው ከሌሎች የልማት ፖሊሲዎች ጋር በማስተሳሰር የህብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው።

ከላይ በቀረበው መሰረት ሀገራዊ ኢኮኖሚው ላይ ዋነኛ ድርሻ ያለው የአለም አቀፍና ሀገር ውስጥ ንግድ የሚወስኑ የሚከተሉት የፖሊሲ ጉዳዮች ተለይተዋል፡፡

5.1 የሀገር ውስጥ ንግድ እና ስርጭት

የጅምላ እና የችርቻሮ ንግድ የሀገር ውስጥ ንግድ የስራ እድልን በማቅረብ፣ የሸቀጦች እና አገልግሎቶች ስርጭትን በማመቻቸት እና የሀገሪቱን የሀገር ውስጥ ምርት እድገት አስተዋፅዖ በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና ያለው ዘርፍ ነው፡፡ እንዲሁም ለተጠቃሚዎች የምርትና አገልግሎቶች ገበያ በማቅረብ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ባለው ትስስር ለኢኮኖሚው ዕድገት ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ በሀገር ውስጥ ንግድ የሚካሄደው የቁጥጥር ሁኔታ በዘርፉ የንግድ ድርጅቶችን የማደግ አቅም ላይ ተጽእኖ በማሳደር እና የቁጥጥር ውስብስብነት ለአገር ውስጥ ንግድ እንቅስቃሴ ቁልፍ ማነቆ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ከፍተኛ መሻሻል የታየበት ቢሆንም፣ ከተዛባ የንግድ ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት አሠራሮች ጋር ተያይዘው የሚመጡ ተግዳሮቶች አሁንም በአገሪቱ የአገር ውስጥ ንግድ ላይ ተፅዕኖ አላቸው፡፡

በብቃት የሚሰራ የሀገር ውስጥ ገበያ ለሀገር ውስጥ ፍጆታም ሆነ ለውጭ ገበያ ምርቶች ልማት እና ስርጭት አስፈላጊ በመሆኑ የሸማቾችን ደህንነት ይጠብቃል፣ያበረታታል፡፡ የስርጭት እና የጅምላ ንኡስ ዘርፍ እድገትና ልማትን እንዲሁም በንዑስ ዘርፉ እና በአምራች ኢኮኖሚው ሴክተር መካከል ያለውን ጎላቀር አሰራር ወደፊት ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የህግ እና የቁጥጥር ሁኔታን ለመፍጠር ያስችላል፡፡ ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ እርምጃዎች ይተገበራሉ፡፡

- አብዛኛው የመጀመሪያ ደረጃ አምራቾችም ሆኑ ሸማቾች ለአደጋ የተጋለጡ በመሆናቸው ሸማቾች የሚከፍሉት ዋጋ እና ለአምራቾች በተለይም ለግብርና እና ለኢንዱስትሪ ምርቶች የሚከፈል ዋጋ መካከል ተገቢ ሚዛን እንዲኖረው ይደረጋል፡፡
- ለአምራቾች ፍትሃዊ የሆነ የዋጋ ተጠቃሚነት እንዲኖር እና በሸማቾችም ያልተገባ የዋጋ ጫና እንዳይኖር ለማድረግ በተመረጡ ዘርፎች ብቻ የመንግስት ጣልቃገብነት ከመኖር ውጭ የነፃ ገበያ ስርዓት እንዲረጋገጥ ይደርጋል፡፡
- የምርት ፍላጎትን ለመጨመር መንግስት የታች ጀምሮ ያለውን የማምረት ሂደትን ያበረታታል፡፡ አመቱን ሙሉ ምርትን በማምረትና በማስተዋወቅ ገቢን ለመጨመር እና አቅርቦትን ለማረጋጋት የሚያስችሉ እርምጃዎችን በመዘርጋት አምራቾችንና ሸማቾችን መሰረት ያደረጉ ድርጅቶችን በመደገፍና በማጠናከር የአምራቾችና የሸማቾችን

የመደራደር አቅም ለማሻሻል እና የአንድ ወገን ፍትሃዊ ያልሆነ ጉዳት እንዲቀንስ ማድረግ።

- ለጅምላና ችርቻሮ ንግድ ንዑስ ዘርፍ ምቹ እና ለንግድ ስራ ተስማሚ የሆነ ሀገራዊ የህግ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ ማዘጋጀት። ሁሉንም የሀገር አቀፍ እና የክልል መንግስታት የንግድ መረጃዎችን እና የንግድ ፈቃድ አገልግሎት የሚያገኙበት ዘመናው አሰራር ስርአት ይዘረጋል።
- መንግስት የንግድ ምዝገባ እና ፍቃድ አሰጣጥን ፍጥነት እና ቅልጥፍናን በኮምፒዩተራይዜሽን እና አሰራርን በማቃለል ያሻሽላል። የአገር ውስጥ ኢንተርፕራይዞች የንግድ ሥራቸውን ለማቋቋምና ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልጉትን አስተዳደራዊ ሂደቶችና ፈቃዶች ያቀላጥፋል። የንግድ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ በሚሳተፉ ሁሉም የሚመለከታቸው ክፍሎች እና ኤጀንሲዎች መካከል ያለውን ቅንጅት በየጊዜው እንዲያድግ ይደረጋል።
- የንግድ መሠረተ ልማትና ሌሎች ፋሲሊቲዎች በስርጭት እና በአገር ውስጥ ዋጋ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። የእንደዚህ አይነት የንገደ መሰረተ ልማት መሳለጥ የምርትና አገልግሎት አቅርቦት፣ የሽያጭ ፍጥነት እና ቅልጥፍናን ያሻሽላል እና ዋጋዎችን ይቀንሳል። ከአምራቾች ወደ ገበያ ለማድረስ እና የትራንስፖርት ወጪን ለመቀነስ መንግስት በቂ እና በሚገባ የተደራጀ የትራንስፖርት እና የሎጂስቲክስ አውታር እንዲሟላ ይሰራል።
- የገበያ ቦታዎችን ማዘመን እና ለሽያጭ እቃዎች ተስማሚ የሆኑ አስፈላጊ መገልገያዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ፣ በተለይም በዋና ዋና ከተሞች እና በልማት ኮሪደሮች ውጤታማ የገበያ መሠረተ ልማት እንዲኖር ይደረጋል። በተጨማሪም በክልሎች መካከል የአገር ውስጥ ንግድን የማመቻቸት ስራ ይሰራል።
- በአገር ውስጥ የሚመረቱ ዕቃዎችን መደገፍ ምርትን፣ የሥራ እድልን እና ሀገራዊ ዕድገትን የሚያበረታታ ፍላጎት ይፈጥራል። እንዲሁም ለአዳዲስ ምርቶች ልማት ወሳኝ ገበያ ያቀርባል፣ የኤክስፖርት አቅምን ይጨምራል። መንግሥት በአገር ውስጥ የሚመረቱ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግብይት እንዲሳለጥ ግንዛቤን ለማሳደግ በአምራቾች፣ ሸማቾች እና ነጋዴዎች መካከል የውይይት አውድ ይመቻቻል። ሀገር በቀል ምርቶችን በሀገር ውስጥ እና በአለም አቀፍ ገበያ እንዲተዋወቁ ይደረጋል።
- በክልሎች መካከል የተሳለጠ ንግድ ለመፍጠር ይሰራል። የሀገር ውስጥ ንግድ መጨመር የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (2ለ) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በክልሎች

ንግድና የውጭ ንግድ ላይ ልዩ ሕጎችን እንደሚያወጣ ይደነግጋል። የሀገር ውስጥ ንግድ መጨመር ለአገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ ሚና ይጫወታል፣ ሀብትንና ጥቅማጥቅሞችን በቀጥታ ወደ አምራቾች እና ሸማቾች እንዲደርስ ይረዳል፣ በክልሎች መካከል ኢኮኖሚያዊ ትስስርን ይፈጥራል እንዲሁም የግጭት እድልን ይቀንሳል። በደንብ ባልተስፋፋ መሰረተ ልማት ምክንያት በክልሎች መካከል ያለውን የንግድ ልውውጥ እንዳስተጓጉል የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ማሻሻል የንግድ ወጪን በመቀነስ የሀገር ውስጥ ንግድን ይጨምራል፣ የውጭ ኢንቨስትመንትንም ለመሳብ የሚያስችል ስራ መስራት አስፈላጊ ነው።

5.2 ለንግድ ስርአቱ ምቹ የማክሮ ኢኮኖሚ ካባቢ

የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ከባቢ መፍጠር የአለም አቀፍና ሀገር ውስጥ ንግድ ስራዎች ለማሳለጥ እና ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ወሳኝ ነው። የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋት በዋነኛነት ዘላቂ እና ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት፣ የተረጋጋ ዋጋና የውጭ ምንዛሬ ተመን፣ የስራ አጥነት መቀነስ እና የተስተካከለ የክፍያ ሚዛን ናቸው። ስለሆነም የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ካባቢን ማስጠበቅ፣ ዝቅተኛ የዋጋ ግሽበት፣ የተረጋጋ የክፍያ ሚዛን እና የውጭ ምንዛሪ ተመን ለዘመናዊ ንግድ ስርአት መገንባት ወሳኝ ጉዳዮች በመሆናቸው የሚከተሉት አቅጣጫዎች ይተገበራሉ።

- ***በሀጋዊ እና በጥቁር የገበያ ምንዛሪ ተመን መካከል ያለውን ልዩነት በማጥበብ ሚዛናዊ የውጭ ምንዛሪ ተመን ስርዓት መፍጠር።*** የሀገሪቱ የዉጭ ምንዛሪ ተመን ፖሊሲ በነጻ ኢኮኖሚ ስርአት ውስጥ የንግድ መጠን እና ዋጋ ለመወሰን ከፍተኛ ሚና ከሚጫወቱት የፖሊሲ መሳሪያዎች አንዱ ነው። ከሌሎች ሀገራት ገንዘቦች አንጻር የብር ምንዛሬ ዋጋ መጨመር ወይም መቀነስ የሀገሪቱን የወጪ ንግድ ምርቶች መጠንና ዋጋ እንዲሁም ለውጭ ሸማቾች ምርቶች ውድ ወይም ርካሽ እንዲሆኑ በማድረግ በውጪ ገበያ ተወዳዳሪነት ላይ ሚና ይኖረዋል። በተጨማሪም የተቀናጀ እና ዓለም አቀፋዊ የማምርት ሂደት እያደገ በመምጣቱ አብዛኛዎቹ አምራቾች የምርት ግብአቶችን ከውጭ በማስመጣት እና ያለቀለት ምርት በማምረት ላይ ስለሚገኙ የውጭ ምንዛሬ ተመን ፖሊሲ በአለም አቀፍ ንግድ ላይ ጉልህ ሚና ይጫወታል።
- **ቀጣይነት ያለው፣ ተገማች እና ግልፅነት ያለው የውጭ ምንዛሬ የአቅርቦት ስርአት መፍጠር።** ሁሉም የወጪና ገቢ ንግድ እና የውጭ ክፍያዎች የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ

ያስፈልጋቸዋል። በመሆኑም የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱ እና አስተዳደሩ ቀጣይነት ያለው፣ ተገማች እና ግልፅነት የሰፈነበት እንዲሁም ከሀገራዊ የልማት እቅድ ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት። ይህ የአሰራር ሂደት ለንግዱ ማህበረሰብ፣ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ባለሀብቶች መተማመንን ይፈጥራል።

- ***የተረጋጋ የዋጋ ሰርአት ለማስፈን በቁርጠኝነት መሰራት፦*** ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት እና የምንዛሪ ተመን ተለዋዋጭነት ለንግዱ ማህበረሰብ እና ለውጭ ባለሃብቶች ንግድና ኢንቨስትመንት ስራዎችን ለማከናወን እንደመስፈርት የሚጠቀሙባቸው ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው። በተጨማሪም የተረጋጋ ዋጋ አለመኖር የሸማቹን የመግዛት አቅም ላይ አሉታዊ ተፅእኖን ይፈጥራል። ስለሆነም የዋጋ ንረትን መቀነስ እና የውጭ ምንዛሬ ክምችትን ማሳደግ ቁርጠኝነትን ስለሚጠይቅ በየደረጃው የሚመለከተው አካ በትኩረት መስራት ይኖርበታል።

5.3 ኢንቨስትመንት እና ንግድ

የወጪ ንግድን ማሳደግ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን መሳብ እና የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንትን ማስፋት የልማት እቅዶችን ለማሳካት በተለይም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረውን የመሪነት ሚና ለማረጋገጥ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት እና ጥራት ያለው እድገት ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው።

የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ሁለት ዋና እይታዎች አሉ። በመጀመሪያ የውጭ ካፒታል በማምጣት ለስራ እድል ፈጠራ እና ለኢኮኖሚ እድገት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል የሚል ሲሆን ሌላኛው እይታ ደግሞ የቴክኖሎጂ እና የእውቀት ሽግግር ለሀገር ውስጥ ድርጅቶች እና ሰራተኞች ማምጣት ነው። የመጀመሪያው የውድድር መንገድ የሀገር ውስጥ ድርጅቶች በአለም ገበያ ተወዳድሮ የገበያ ድርሻን ማስጠበቅ ነው። ሁለተኛው የማሳያ መንገድ ደግሞ የሀገር ውስጥ ድርጅቶች የማምረት ሂደቶችን የሚማሩበት፣ የአመራር ልምድን የሚያዳብሩበት እና በቴክኖሎጂ ሽግግርን ከውጭ ኩባንያዎች የሚቀስሙበት የጎንዮሽ ጠቀሜታዎችን ማግኘት ነው። የቴክኖሎጂ እና የእውቀት ሽግግር ከውጭ ድርጅቶች ወደ ሀገር ውስጥ ድርጅቶች ለማስተላለፍ ግልፅ የሆነ የንግድ፣ ኢንቨስትመንት እና የኢንዱስትሪ ፖሊሲዎች ያስፈልጋሉ። እነዚህ መንገዶች አስፈላጊ ቢሆኑም ተጨባጭ የሆነ የኢኮኖሚ

ጥቅሞች የሚገኙት ቀጥተኛ በሆነ ትስስር የሀገር ውስጥ ድርጅቶች ከውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ግብዓቶችን የሚያቀርቡበት ሁኔታ ሲመቻች ነው።

ሀገሪቱ ከሌሎች ሀገራት ጋር ተወዳዳሪ ሆና የውጭ ኢንቨስትመንት ለመሳብ የሚያስችል ሊሰለጥን የሚችል የሰው ኃይል፣ ከፍተኛ ዋጋ ያለው የማዕድን ክምችት፣ ተስማሚ የአየር ንብረት ያለው ሰፊ መሬት እና የተለያዩ የግብርና ስነ-ምህዳር (agro-ecology) ሀብቶች አሏት። በመሆኑም መንግስት ከግሉ ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀትና በማጠናከር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን ለማሳደግ የሚያስችል ስርአት ዘርግቷል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በየጊዜው የሚደረጉ የፖሊ ማሻሻያ ዋነኛ ነጥቦች ተቋማዊ ለውጥን በማምጣት ቅንጅታዊ ጉድለቶችን መፍታት እና ለንግድና ኢንቨስትመንት የሚረዱ የህግ ማዕቀፎችን ማጠናከርና ማሻሻል ይጠይቃል። የመጀመርያው የንግድ ስርዓቱን ቀላል በማድረግ የሙስናና የኪራይ ሰብሳቢነት አድማሱን መቀነስ ሲሆን ሁለተኛው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የሚስቡ እና አለም አቀፍ፣ ቀጣናዊና የሁለትዮሽ ስምምነት ጋር በመጣጣም ንግድና ኢንቨስትመንትን ማበረታታት ናቸው። በመሆኑም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል።

- የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ አዲሱን የኢንቨስትመንት አዋጅና ደንብ በአግባቡ መተግበር። እ.ኤ.አ. በ2020 በተሃድሶው አጀንዳ መሰረት የኢትዮጵያ መንግስት አዲስ የኢንቨስትመንት አዋጅ እና ደንብ (ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 1180/2020) አጽድቋል። አዲሱ ደንብ የውጭ ባለሀብቶች የሚሳተፉባቸውን የኢንቨስትመንት ዘርፎች የያዘ ነው። ይህ አዲስ ማዕቀፍ የኢንቨስትመንት አስተዳደር ስርዓቱ ግልፅ፣ተገማች እና ቀልጣፋ እንዲሆን ያስችለዋል፣ በመሆኑም በኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት መስህብ፣መቆየት እና መስፋፋትን የሚያበረታታ ሁኔታን ይፈጥራል። ከዚህ ባለፈም በአዲሱ አዋጅ ቅሬታዎችን እና የኢንቨስትመንት አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያስችል አሰራርን አስቀምጧል። አዲሱ የኢንቨስትመንት ህግ በርካታ ዘርፎችን ለውጭ ኢንቨስትመንት ነፃ የሚያደርግ እና ከመንግስት ወይም ከአገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር የጋራ ኢንቨስትመንትን ያበረታታል።
- የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የብሔራዊ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ፖሊሲን በአግባቡ መተግበር። እ.ኤ.አ. በ2022 መንግስት የአለም አቀፍ ንግድ እና አህጉራዊ ውህደት

ለአገሪቱ የልማት ግብ ያለውን ጠቀሜታ የሚያጎላ የብሔራዊ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ፖሊሲን አፅድቋል። የልዩ ኢኮኖሚክ ዞኖች ልማት መንግስት የሀገሪቱን የንግድ ተወዳዳሪነት ለማሻሻል፣ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን ለማሳደግ እና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ከሚጠቀምባቸው ቁልፍ የፖሊሲ ውጥኖች አንዱ ነው። በእስያ ያለው የሰው ሃይል ዋጋ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ኢትዮጵያ እንደ ጨርቃጨርቅ ያሉ የሰው ሃይል የሚጠይቁ ኢንዱስትሪዎች መዳረሻ ትሆናለች ተብሎ ይታመናል። የበርካታ አገሮች ልምድ እንደሚያሳየው የልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ስኬት በከፍተኛ ሁኔታ ላይ የተመሰረተው በተቀናጀ ከፍተኛ የመንግስት ድጋፍ የሀገሪቱን አንጻራዊ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ እና እንከን የለሽ ቅንጅት በመላው የመንግስት መ/ቤቶች ላይ በትክክል በመስራት ላይ የተመሰረተ ነው።

- ከሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ጋር ግንኙነት ለሚፈጥሩ የውጭ ኩባንያዎች የማበረታቻ ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ ነው። ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ኩባንያዎች የሚሰጡት ጥቅም የኋልዮሽ እና የወደፊት በሚደረጉ ግንኙነቶች የሚመሰረት ነው። የኋልዮሽ ትስስር የሚፈጠረው የሀገር ውስጥ ድርጅቶች ግብአቶችን ሲያቀርቡ እና ወደፊት ትስስሮች ደግሞ የሀገር ውስጥ ድርጅቶች በአስተናጋጅ ሀገር ውስጥ ከሚገኝ አለም አቀፍ ድርጅቶች(multinational companies) ግብአት ሲገዙ ነው። የአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጣና በአገሮች መካከል የኢኮኖሚ ትስስርን ለማመቻቸት የተነደፉ ሲሆኑ ከሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ጋር ግንኙነት ለሚፈጥሩ የውጭ ኩባንያዎች የተለያዩ ማበረታቻዎችን መስጠት አስፈላጊ ነው።

- ***የሀገር ውስጥ ድርጅቶች አቅም ለማጠናከር የገንዘብ እና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት።*** እውቀት እና ቴክኖሎጂ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ኩባንያዎች እንዲሸጋገሩ የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች አዳዲስ እውቀቶች እና ቴክኖሎጂዎች ወደ ምርት ሂደታቸው የማዋሃድ አቅም ሊኖራቸው ይገባል። እንደ ፈጠራ ፈንድ፣ የአቅራቢ ልማት ፕሮግራሞች፣ የክህሎት ማሻሻያ ማበረታቻዎች፣ እርዳታዎች፣ ብድር እና የሥልጠና ወጪዎች፣ የቴክኖሎጂ ግዥ እና ሙያዊ አገልግሎቶች በተለይም ለሀገር ውስጥ ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሂደቱን ያመቻቻል። በተጨማሪም የኩባንያዎችን የአስተዳደር፣ የምርት፣ የሽያጭ እና የንግድ ስራ ፈጠራ እና የሰው ሃይል አቅም የሚያሻሽሉ የሀገር ውስጥ

ድርጅቶች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት የኩባንያዎችን ቴክኖሎጂን የመጠቀም አቅም ይጨምራል።

5.4 የንግድ ወጪን መቀነስ እና አለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ

አስተማማኝ ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ዘርፍ ለአለም አቀፍ ንግድ እና ልማት ወሳኝ ነው። በተለይም የባህር በር ለሌላቸው ሀገሮች እና እንደ ኢትዮጵያ ያሉ 90% የሚሆነው ንግድ በየብስ ትራንስፖርት ለሚያከናውኑ ሀገሮች ጠቀሜታው የጎላ ነው። በአሁኑ ወቅት ያለው የሀገራችን ሎጀስቲክስ ዘርፍ በሚገባ ያላደገ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ በተገቢው ሁኔታ ውጤታማ ያልሆነ የሎጀስቲክ ስርዓት እና በቂ ያልሆነ ተርሚናል አገልግሎት የሚታይበት ነው። ይህም በአለም አቀፍ ንግድ ላይ የሚሳተፉ የንግድ ተዋናዮች ላይ የንግድ ወጪዎችን የሚጨምር ሲሆን በአለም አቀፍ ገበያዎች ላይ ያላቸውን ተወዳዳሪነትም ይቀንሳል። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት እነዚህ የንግድ ወጪዎች በምርቶች የመጨረሻ ዋጋ ላይ ከ20-27% ይጨምራል። የሀገራችን የማንገዝ እና የጭነት ወጪም ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ሲነጻጸር 60% ያህል ይጨምራል። ተወዳዳሪ እና ውጤታማ የሆነ የሎጀስቲክስ ዘርፉ የወጪ እና ገቢ ንግድ ላይ የተሰማሩ የንግዱ ማህበረሰብ ጨምሮ አጠቃላይ የግሉን ዘርፍ ተወዳዳሪነት ለማሻሻል የሚረዳ ነው። የኢትዮጵያ የልማት እቅዶች የሎጀስቲክስ ስርዓት ለማዘመን እና ለማሻሻል እንዲሁም የመሰረተ ልማት ስራዎች በንግድ እቃዎች መተላለፊያ ኮሪደሮች ጋር በማስተሳሰር ምርትና ምርታማነትን በኢኮኖሚ ውስጥ ማሳደግ ነው።

- ***መንግስት የሎጀስቲክስ ዘርፉን ቅድሚያ መስጠትና ክትትል ማድረግ እንዲሁም የፋይናንስ አቅርቦት በማድረግ የታቀደውን የሎጀስቲክስ ዘርፍ ማሻሻያ በፍጥነት መተግበር።*** በአሁኑ ወቅት መንግስት የሎጀስቲክስ ዘርፉን ለማሻሻል ሶስት ዓላማዎች ያሉት እቅድ ተግባራዊ እያደረገ ሲሆን በዋነኝነት የሎጀስቲክስ ዘርፉን ተወዳዳሪነትና ውጤታማነት ማሳደግ፤ ሎጀስቲክስ እና ተያያዥነት ያለቸውን አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ ማድረግ እና በሎጀስቲክስ ዘርፉ ውስጥ ያሉ የመንግስትና የግሉ ተዋናዮችን ቅንጅት ማሳደግ ናቸው። በዚህ ሂደት በርካታ እርምጃዎች እየተወሰዱ ቢሆንም መንግስት እነዚህን ሪፎርሞች እና ትግበራዎች በፍጥነት ማካሄድ እና በቀጣይነት የዓለም ሁኔታውን ባማከለ አግባብ ማሻሻል አስፈላጊ ነው።
- ***የግል ዘርፉ በሎጀስቲክ ዘርፉ እንዲሳተፉ እና ተወዳዳሪና አዳዲስ ፈጠራዎች እንዲያመጡ ማበረታታት።*** መንግስት የሎጀስቲክ ዘርፍ ለውጭ አገር አገልግሎት ሰጪዎች ከሀገር

ባለሀብቶች ጋር በጭነትና አስተላላፊነት ዘርፍ በጥምረት መስራት እንዲችሉ ፈቅዷል። በቀጣይም የኢኮኖሚ ሁኔታውን በመመልከት ደረጃ በደረጃ የባህር ትራንስፖርት ዘርፉን እና መልቲሞዳል የትራንስፖርት ዘርፉን በማዘመን የአቅርቦት ሰንሰለቱን በማሳጠር በጊዜና በወጪ ረገድ ተጠቃሚ ለመሆን የሚረዳ አሰራር ይከተላል።

- ***በትራንዚት ኮሪደሮች እና በባህር ወደቦች የሚያደረገውን ኢንቨስትመንት በማጠናከር የውጪና የገቢ ንግድ በመጠንና በአይነት የሚሳለጥበት ሁኔታ ማመቻቸት።*** በቀጣይ የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ በውስን የባህር ወደቦች ላይ ያለውን ጥገኝነት በመተው የተለያዩ የንግድ መስመሮችን በመጠቀም ከሀገራት የሚደረገውን የንግድ ድርድሮች የተሻለ የመደራደር አቅምን ከፍ ያደርጋል።
- የሎጅስቲክ ዘርፉ በውስጡ በርካታ ተዋናዮችን እና ተቋማትን የሚያካትት ሲሆን ለአብነትም የባህር ትራንስፖርት፣ የመንገድ ትራንስፖርት፣ የባቡር ትራንስፖርት፣ ወደቦች፣ ጉምሩኮች፣ ፋይናንስ እና ከንግድ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተቋማት የሚይዝ ነው። ስለሆነም በእነዚህ ቁልፍ ተዋናዮች ዙሪያ የተቀናጀ ትብብር ማድረግ እና ስራዎች የሚያከናወኑበት መመሪያ ማውጣት እና የሚደራረቡ የተቋማት ስራዎችን መቀነስ የሚገባ ነው።

የንግድና ኢንቨስትምንት ማሳለጥ ስራዎች የግል ኢንተርፕራይዞችን ወጪ ይቀንሳል፣ ተወዳዳሪነታቸውን ይጨምራል እንዲሁም የአለም አቀፍ ንግድ ተሳትፎን ያሳድጋል። የንግድ ማሳላጥ ማለት የቴክኒክ እና የህግ ሂደቶችን ማቅለልና ምቹ ማድረግ፣ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥን በአቅርቦት ሰንሰለት ተዋናዮች ዙሪያ ማስፈን፣ የንግድ ሰነዶችን ከንግድ አጋሮች ጋር ማውሃድና ማቅለል፣ በክፍያዎች ላይ ግልጸኝነትን ማስፈን እንዲሁም በህጎችና መመሪያዎች ላይ ግልጽነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። ከሁለት መንግስታት፣ በቀጣናዊ እና ከዓለም መንግስታት ጋር የሚደረጉ የንግድ ስምምነቶች የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነትን ጨምሮ በከፍተኛ መጠን የንግድ ማሳለጥ እርምጃዎችን ለመውሰድ ከፍተኛ ድጋፍ ይሰጣሉ። በተጨማሪም የንግድ መሳለጥ የውጪ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጸ ያበረክታል።

ከሁሉም ይበልጥ የንግድ ማሳለጥ ስራ የንግድ ወጪው በተነጻጻሪነት ከፍተኛ በሚሆንባቸው አነስተኛ፣ የጥቃቅን እና የመካከለኛ ደረጃ ባላቸው ኢንተርፕራይዞች ላይ ማተኮር አለበት። የንግድ ማሳላጥ በተለይም የሚበላሹ የግብርና ምርቶች ለሚያመርቱ አካላት ጊዜ በጣም ወሳኝ

በመሆኑ ትኩረት መስጠት ያሻል፡፡ በመጨረሻም የንግድ ሂደቶችን ማቅለል የኢኮኖሚ ውጤታማነት የሚያሳድግ እንዲሁም ከድንበር ጋር የተገናኙ የሙስና ተግባሮችን የሚቀንስ ስለሆነ መልካም አስተዳደርን በቁርጠኝነት ማስፈንን ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም የሚከተሉት ተግባራት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፡፡

- ሀገራዊ ንግድን ለመጨመር የሚረዱ የንግድና ኢንቨስትመንት የዓለም አቀፍ፣ የቀጣናዊ እና የሁለትዮሽ ስምምንቶች በየጊዜው በማጥናት ሀገራዊ ጥቅምን በሚያረጋግጥ ሁኔታ መተግበር፤
- ከጎረቤት ሀገራት ጋር የጉምሩክ ትራንዚት ስምምነቶች በመፈጸም የጉምሩክ እቃዎች ዝውውር በአካል ተገኝተው የመፈተሽ ስልጣናቸውን በመወሰን እና በድንበር ተሻጋሪ ንግዶች የትራንዚት እና የአሰራር መመሪያዎች የማሻሻያ ሀሳችን ማውጣትና መተግበር፡፡
- ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች የቴክኒክ እና የአቅም ግንባታ ድጋፎች በመጠቀም የጉምሩክ ክሊራንስ መሰረተ ልማቶችን መገንባት እና የማስፋፊያ ስራዎችን ማከናወን፡፡
- የኢንቨስትመንት እርምጃዎችን ግልጽነት ማሻሻል፣ የስራ ክፍፍል መፍጠር እና የአስተዳደር ሂደቶችን ማፋጠን እንዲሁም አለም አቀፍ ትብብሮችን ማጠናከርና የኢንፎርሜሽን ልውውጥ ማድረግ እና ምርጥ ተሞክሮችን መጋራት፡፡
- አብዛኛው የወጪ ንግድ ምርቶች የግብርና ምርቶች በመሆናቸው የግብርና ንግድ ማሳለጥ ወሳኝ በመሆኑ ትኩረት የሚያስፈልገው ነው፡፡ ስለዚህ ዘመናዊ የእንሰሳት፣ የእጽዋትና የሰው ጤና የማይጎዱ የደረጃ መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስችሉ ላብራቶሪዎችን እና መፈተሻዎችን በማዘጋጀት፣ አለም አቀፍና ሀገራዊ ደረጃዎች በማውጣት እና ላብራቶሪዎች አክሪዲትድ በማድረግ የወጪ ምርቶች ዓለም አቀፍ ደረጃዎች እንዲያሞሉ መስራት አስፈላጊ ነው፡፡

5.5 የገበያ ተደራሽነትን ማስፋት

የገበያ ተደራሽነትን ማስፋት ለሀገራችን የወጪ ንግድ ስርአት ዋነኛ መሰረት ነው፡፡ የሀገራችን የወጪ የምርቶችና አገልግሎቶች በተለያዩ የመዳራሻ ገበያዎች የሚያጋጥማቸውን ታሪፍና ከታሪፍ ውጪ የሆኑ እርምጃዎች ላይ ትኩረት ይደርጋል፡፡፡ የገበያ ተደራሽነትን የሚወስነው ሀገራችን የምታደርጋቸው የባለብዙ ዘርፍ እና የሁለትዮሽ ንግድና ኢንቨስትምነት ስምምነቶች

እንዲሁም የሚገኙ የንግድ ትስስር እድሎች የስሪት ሀገር ምንጭ መስፈርቶች ማሟላት ሲኖርባቸው ነው፡፡ ለወጪ ንግድ አፈጻጸም ተግዳሮቶች የሚሆኑት በአቅርቦት በኩል ያለው ድክመት ቢሆንም ለሀገራችን ኤክስፖርት መር የንግድ ፖሊሲ ውጤታማ ለመሆን በበለጸጉትም ሆነ በታዳጊ ሀገሮች ሰፊ የገበያ እድል ማግኘት ወሳኝ ነው፡፡

ከፍተኛ የሆነ ታሪፍ እና ከታሪፍ ውጪ ያሉ መሰናክሎች የውጪ ምርቶች በገበያ መዳረሻዎች ላይ ያላቸውን ተወዳዳሪነት ይቀንሳል፡፡ በተለይም ከታሪፍ ውጪ ያሉ እርምጃዎች ከልካይ ደንቦች፣ መስፈርቶች፣ ፍተሻና ፈቃድ (በዋነኝነት የእንሰሳት፣ የእጽዋትና የሰው ጤና) እና የንግድ ቴክኒክ መሰናክል እርምጃዎች ለሀገራችን የወጪ ንግድ ጉልህ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ናቸው፡፡ የታሪፍም ሆነ ከታሪፍ ውጪ ላሉ መሰናክሎች ለማስወገድ የተለያዩ መንገዶች ያሉ ሲሆን እነሱም ከመንግስታት ጋር የሚደረግ ዓለም አቀፍ፣ ቀጣናዊ እና የሁለትዮሽ የንግድ ስምምነት መፈጸም ዋነኛው መፍትሄዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም የሚከተሉት አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

- **የዓለም ንግድ ድርጅት በአባልነት-ለመቀላቀል የሚደረገው ድርድር መጨረስና ስምምነቱን ተግባራዊ ማድረግ፡፡** ኢትዮጵያ በይፋ የአለም ንግድ ድርጅትን ለመቀላቀል በ1995ዓ.ም ጥያቄ ያቀረበች ቢሆንም በድርጅቱ ውስጥ ለመቀላቀል አስፈላጊ የሆኑ ሪፎርሞች በመዘግየታቸው ምክንያት እስከአሁን ድረስ አባል መሆን አልቻለችም፡፡ በአሁኑ -ወቅት የዓለም ንግድ ድርጅት ለመቀላቀል የሚደረገው ሂደት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ የዓለም ንግድ ድርጅትን መቀላቀል ለሀገራችን ኤክስፖርት ከሌሎች የዓለም ንግድ ድርጅት አባል አገራት እኩል የገበያ ዕድል እንዲያገኙ ያስችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሀገራችን ነጻ የንግድ ስምምነት ስታደርግ መንግስት የሚያገኘውን የታሪፍ ክፍያ ገቢ የሚያሳጣው ይሆናል፡፡ ለምሳሌ የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና 90% የሚሆነውን ታሪፍ በአስር ዓመት ነጻ መደረግ ያለበት ሲሆን 7% የሚሆነው ታሪፍ ደግሞ ከ5 ዓመት የሽግግር ጊዜ በኋላ ነጻ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በጥቅሉ በ13 ዓመታት 97 % የሚሆነው የታሪፍ መስመር ለአፍሪካ ገበያ ነጻ የሚሆን ሲሆን የታሪፍ ገቢ የሚቀንስ እና መዳረሻ ገበያን የሚያሰፋ ይሆናል፡፡
- **የቀጣናዊ ንግድ ስምምነቶችን በማድረግ በቀጣናዉ ያለውን የንግድ ትስስሮች ማጠናከር፡፡** ሀገራችን የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጣና ስምምነት የፈረመች እና ያጸደቀች ሲሆን ይህ ስምምነት ዓላው በአፍሪካ ሀገሮች መካከል የንግድ ታሪፍን ቀስ በቀስ ማስወገድ ነው፡፡

በዚሁ ስምምነት አባል ሀገራት 90% የሚሆነው የታሪፍ መስመር በእድገት ወደ ኃላ የቀሩ ሀገሮች በ10 ዓመት ውስጥ ነጻ ለማድረግ እንዲሁም የተቀሩት አገሮች በ5 ዓመት ነጻ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። 7% የሚሆነው ታሪፍ መስመር እቃዎች ላይ በረጅም ጊዜ ሊበራላይዝ እንዲደረጉ ማለትም በልማት ወደኋላ ለቀሩ ሀገሮች በ13 ዓመት እንዲሁም ለተቀሩት በ10 ዓመት ታሪፋቸውን ዜሮ ማድረግ ይኖርባቸዋል ። ቀሪው 3% የታሪፍ መስመር ከታሪፍ ሊበራላይዜሽን ለጊዜው ውጪ ቢሆንም በየአምስት አመቱ የምርቶቹ ሁኔታ የሚታይ ነው። የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና በወጪ ንግድ ላይ ለተሰማሩ የንግድ ስራዎች የውጪ ገበያ የሚከፍት ቢሆንም በተመሳሳይ ደግሞ የሀገር ውስጥ ገበያን ለውጪ አገር ምርቶች ተፎካካሪነት የሚያጋልጥ ስለሆነ ምርታማነትን እና በንግድ ስራ ውጤታማነትን ማሳደግ የሚጠይቅ ነዉ።

- **በዓለም አቀፍ፣ በቀጣናዊ እና በሁለትዮሽ የሚፈረሙ እና ተግባራዊ የሚደረጉ ስምምነቶች ከሀገር ውስጥ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ጋር ማጣጣም።** ሀገራቱ ከበርካታ መንግስታት ጋር ካደረገቻቸው የንግድና ኢንቨስትመንት ስምምነቶች በተጨማሪ የአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት ፈርማለች። ስለሆነም የኢንቨስትመንት ስምምነቶች እያንዳንዱን ከሀገራችን ህጎችና ስምምነቶች መቃኘት እንዲሁም በዓለም ንግድ ድርጅት ውስጥ እና በሌሎች ቀጣናዊ ስምምነቶች ውስጥ ያሉ ግዴታዎችን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል። ሀገራችን የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና የኢንቨስትመንት ፕሮቶኮል ስምምነት የተቀበለች ሲሆን ተጠቃሚ ለመሆን ሀገሪቱ በግልጽ የተነደፈ ፖሊሲዎች፣ ዓላማዎች እና ስትራቴጂዎች ማረጋገጥ ወሳኝ ነው።

- **ኢ-መደበኛ የሆኑ የድንበር ላይ ንግዶች ወደ መደበኛ የንግድ ስራዎች እንዲሰማሩ ማድረግ።** የዓለም ንግድ ስርዓት እንደሚያሳየው ሀገሮች በተለይም ድንበር የሚጋሩ ወይም በቅርበት የሚገኙ ሀገሮች በርቀት ከሚገኙ ሀገሮች ይልቅ የበለጠ የንግድ ትስስር ይኖራቸዋል። በአሁኑ ወቅት ሀገራችን ያጸደቀችው የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት የንግድ መጠኑን የመጨመር እና ህገ-ወጥ ንግድ የመቀነስ እድል ይኖረዋል። ስለሆነም በጥናት ላይ ተመስርቶ ይፋዊ ባልሆነ የድንበር ንግድ ላይ እንዲሰማሩ ያደረጓቸውን ገፊ ምክንያቶች በተለይም ረጅም ቢሮክራሲ፣ በቂ ያልሆነ መሰረተ ልማት፣ የማበረታቻ እጦት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል። በተለይም አነስተኛ ፣

ጥቃቅን እና መካከለኛ ደረጃ ያላቸውን ኢንተርፕራይዞች በንግድ ፖሊሲው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ስትራቲጂዎች መንደፍ ይጠይቃል፡፡

- የገበያ እድሎች እና ከታሪፍ ውጪ ያሉ የንግድ መሰናክሎችን መለየት እና መፍታት፡፡ እነዚህን ስራዎች በሀገራችን ኢምባሲዎች በኩል የሚከናወኑ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ሀገራችን በእያንዳንዱ የመዳረሻ ገበያዎች በኤክስፖርተሮች ላይ የሚፈጠሩ ተግዳሮቶችን መለየት እና መረጃዎችን በኢምባሲዎች በኩል ማደራጀት እና ችግሮችን የመፍታት ስራ ይሰራል፡፡
- የቴክኒክ እና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግ፡፡ የንግድ ስምምነቶች በገበያ ላይ ለሚልኩትና ለሚያስመጡት ምርት በቅናሽ ታሪፍ እንዲስተናገዱ የሚያደርጋቸው ነው፡፡ ለምሳሌ የሀገሮች ድርጅቶች የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን የስሪት ሀገር ምንጭ መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ የሀገራቱ መስፈርቶችና ህጎች ውስብስብ በመሆናቸው በተለይ ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በቀላሉ ለመረዳት ይቸገራሉ፡፡ በመሆኑም የንግድ ፖሊሲው ስኬታማ እንዲሆን የንግዱ ማህበረሰብ ስለ ህጎችና ደንቦች እንዲያውቁ ማድረግና አዲስ የንግድ እድሎችን ለመጠቀም እንዲችሉ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም ለንግድ ውድድር የበለጠ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ማለትም ነጋዴ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ልዩ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ለንግዱ ማህበረሰብ ተፈላጊ የሆኑ ህጎችን የሚያሳውቁ ድረ ገጾችን እና የመረጃ ዴስኮች ማደራጀት ስራ ይሰራል፡፡

5.6 የወጪ ንግድ ብዝሀነት

ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችና አገልግሎቶች ስርጭትና ብዛት፣ የምርት አይነቶች እና የመዳረሻ አገሮች የኤክስፖርት ገበያ ብዛት ዉጫዊ ስጋት እና ተጋላጭነትን ይቀንሳል፡፡ ይህ በተለይ ለኢትዮጵያ ጠቃሚ የሚያደርገው አብዛኛዉ የወጪ ንግድ የአየር ንብረት መለዋወጥ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ እንደ ቡና፣ ሰሊጥ እና ጫት ያሉ የግብርና ምርቶች ከሚመነጨዉ የአለም አቀፍ የግብርና ምርቶች ዋጋ መዋዠቅ ምክንያት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ በርካታ ፈተናዎችን እና ስጋቶችን ይፈጥራል፡፡ የኢትዮጵያ ወጪ ንግድ ብዝሃነት የአቅርቦትን ችግር እና የፍላጎትን ውስንነት ችግር መፍታት አለበት፡፡

በምርቶች ንግድ ላይ ካለዉ ብዝሀነት በተጨማሪ የአግልግሎት ዘርፍ ለአገሪቱ የወጪ ንግድ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለዉ፡፡ የኤክስፖርት ስትራቴጂው ቱርዚምን፣የኤሌክትሪክ ሃይል፣

ትራንስፖርት፣ሎጀስቲክስን እና ሙያዊ አገልግሎቶችን እንደ ትልቅ እድሎች ተለይቷል። የአገሪቱን የቱሪስት ስፍራዎች ውበት እና ተደራሽነት ለማሳደግ የሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች የቱሪስት አገለግሎት አቅርቦትን በማዘመን አዳዲስ መስህቦችን በማልማት ነባሮቹን በማስተዋወቅ ረገድ ወሳኝ ናቸዉ። ወደ ጎረቤት ሀገራት የመላክ አቅም ያለዉ ሀይድሮ ኤሌክትሪክ ግድቦች፤ የፀሀይ ሙቀት ማመንጫ ጣቢዎች እና የጂኦተርማል ማመንጫ ጣቢዎች ግንባታ ሲጠናቀቁ ለውጭ ገበያ የሚቀርበው የኤሌክትሪክ ሀይል መጠን ይጨምራል።

የሀገራችን የፕሮፌሽናል አገልግሎት ኤክስፖርት በአንፃራዊ ሁኔታ ሲታይ አነስተኛ ቢሆንም በዋናነት ከፊል ሙያዊ አገልግሎቶች እና የሰለጠነ ሙያዊ አገልግሎቶች (ከኢትዮጵያ አየር መንገድ እና የባህር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት) ወደ ዉጪ መላክ የሚያስችል ሰፊ እድል አለ። ስለሆነም መንግስት ሁሉን አቀፍ የኤክስፖርት ልማት ስትራቴጂ የሚዘረጋ እና የሚፈጽም ይሆናል። የገበያ ተደራሽነትን ለማስፋት መስራት ማለት በሁሉም መንገድ ማለትም ወደላይ በአንድ ሴክተር የእሴት ሰንሰለት በማሳደግ እና ወደ ጎን በሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት ላይ ከመጠን በላይ ጥገኛ ያልሆኑ አዳዲስ እንዱስትሪዎችን በማስፋፋት መስራት ይገባል።

5.7 በአለም አቀፍ እሴት ሰንሰለት ዉስጥ መሳተፍ

ባለፉት ጥቂት አስርት ዓመታት የአለም ምርት ሂደት በተለያዩ አገሮች በከፍተኛ ደረጃ የተበታተነ እና የተሰራጨ ነው። መሪ በሆነው አምራች ድርጅቶች አማካኝነት የማምረት ስራ በርካታ ድርጅቶች የሚያሳትፉ መሆኑ እየጨመረ ሲሆን በድርጅቶች መካከል ያለዉን ትብብር የሚያሳልጡ የተለያዩ የኮንትራት እና የአጋርነት አሰራሮች አሉ። በዚህ ምክንያት የድርጅቶች በአለም አቀፍ የእሴት ሰንሰለቶች (global value chain) ዉስጥ መሳተፋቸው፤ ከፍተኛ ዋጋ ሊያስገኙ የሚችሉ እሴት የተጨመረበት የወጪ ምርት ለማቅረብ፣ ምርታማ የሆነ ኢንቨስትምንት እንዲኖር እና አካታችና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት እንዲመጣ የማድረግ አቅም ይፈጥራል። የተሳካ በአለም አቀፍ እሴት ሰንሰለት ዉስጥ ተሳትፎ ለማድረግ የተለያዩ ሀገራዊ ኢኮኖሚ ልማት ግቦች ማሻሻዎች የሚያስፈልገዉ ሲሆን፤ የንግድ ፖሊሲ የሀገሪቱን ንግድና ኢኮኖሚ ከአለም አቀፍ ምርት ሂደት ጋር የሚኖረዉን ትስስር ለማሳለጥ ያስችላል።

- ከአንፃራዊ ጠቀሜታ ትንተና ዘዴ ይልቅ በጥልቅ ትንተና ላይ የተመሰረተ ጥናት በማካሄድ ቅድሚያ የሚሰጣቸዉን ዘርፎች በመለየት መስራት አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ በቆዳና ቆዳ ውጤቶች እንዱስትሪ ዉስጥ ያለዉን አጠቃላይ የምርት ሂደት ከጥሬ ቆዳ ጀምሮ፣ከፊል ተዘጋጅቶ የተሰራ ቆዳ፣ ያለቀለት ቆዳ፣ የቆዳ ክፍሎች (leather

components) እና የቆዳ ውጤቶችን እሰከ መጨረሻው ድረስ በመለየት ሀገሪቱ የት ላይ መሳተፍ እንደምትችል ይለያል፡፡ ቅድሚያ በሚሰጣቸዉ ዘርፎች አጠቃላይ የምርት ሂደቱን መተንተን የአገር ዉስጥ ኩባንያዎች በእሴት መጨመር ላይ ዉጤታማ በሆነ መንገድ የሚሳተፉባቸዉ ቦታዎች ለመለየት ያስችላል፡፡

- በአለም አቀፍ እሴት ሰንሰለት (GVC) ተሳትፎን ለማሳለጥ ሀገሪቱ በአለም አቀፍ ደረጃ የገበያ ተደራሽነትን ማሻሻል እና ከዋና ዋና የንግድ አጋሮች ጋር ያለዉን የኢኮኖሚ ትስስር ማጠናከር ይገባል፡፡ የአለም አቀፍ እሴት ሰንሰለት (GVC) የተመሰረተው በድንበር ተሻጋሪ የንግድ ፍሰት ነዉ፡፡ በመሆኑም የንግድና የኢንቨስትመንት መሰናክሎችን ማስወገድ፣ ጥልቅ የንግድ ስምምነቶችን መፈረም እና ድንበር ዘለል የቁጥጥር ማዕቀፎችን የማጠናከር ስራ ይሰራል፡፡
- ወደ ሀገር ዉስጥ የሚገቡ የምርት ግብአቶች ሁኔታ የማመቻቸት ስራ መስራት፡፡ በአለም አቀፍ እሴት ሰንሰለት (GVC) ዉስጥ ለመሳተፍ ጥራት ያለው ምርት ማምረት ያፈልጋል፡፡ ድርጅቶች ጥራት ያለዉ ምርት ለማምረት ከወጪ የሚገቡ ጥራት ያላቸዉ ግብአቶችን ማግኘት ያስፈልገቸዋል፡፡ የነፃ ንግድ ስምምነቶች መሻሻል በሸቀጦች እና አገልግሎቶች ላይ ከታሪፍ ውጪ የሆኑ እንቅፋቶችን ዝቅ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡
- በአለም አቀፍ እሴት ሰንሰለት (GVC) የሚመራ ልማት ስኬታማ እንዲሆን የመንግስት እና የግል አጋርነት (PPP) ማጠናከር አስፈላጊ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ የአስር አመት የልማት ዕቅድ ስትራቴጂካዊ ምሰሶዎች አንዱ በኢኮኖሚ ዉስጥ የግሉን ዘርፍ አመራር ከፍ ለማድረግ ጠንካራ የመንግሰት እና የግል አጋርነት በመፍጠር በገበያ የሚመራ ኢኮኖሚ መገንባት ነው፡፡ የመንግሰትና የግል አጋርነት ፋይዳን በመገንዘብ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት ለመደገፍ እና የህዝብ አግልግሎቶችን ጥራት ለማሻሻል በተለይም በመሰረተ ልማት ላይ ዘርፉን ለማጠናከር የመንግሰትና የግል አጋርነት ወሳኝ ነዉ፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያየመንግሰትና የግል አጋርነት በአዋጅ ቁጥር 1076/2018 ወጥቷል፡፡ ስለዚህ በረጅም ጊዜ የመንግስትና በግል አጋርነት የቴክኖሎጂ ክህሎት በመጨመር ምርትን ለማሳደግ ይበልጥ አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡
- የላቀ የአለም አቀፍ እሴት ሰንሰለት (GVC) ተሳትፎ ለማረጋገጥ ትስስርን እና የአቅራቢዎችን አቅም የማሳደግ ስራ ይሰራል፡፡

- በአለም አቀፍ እሴት ሰንሰለት (GVC) ውስጥ ሀገራዊ ድርጅቶች ጠንካራ ትስስር ለመፍጠር ለአንስተኛ እና ለመካክለኛ ኢንተርፕራይዞች ፋይናንስ ድጋፍ ማድረግ ይገባል። ድርጅቶች ለረጅም ጊዜ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅራቢ ልማት ፕሮግራም (supplier development programs (SDPs)) በማመቻቸት ተጨማሪ ኢንቨስትመንት በማድረግ የምርቶችን ጥራት እና ደረጃዎች እንዲያሻሽሉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም የንግድ ድርጅቶች አዳዲስ ፈጠራዎችን እንዲያወጡ እና ከወጪ ድርጅቶች ጋር ሽርክና ለመፍጠር የሚያስችል የአቅም ግንባታ ድጋፍ እጅግ አስፈላጊ ነዉ።
- የአግልግሎት ንግድ በአለም አቀፍ እሴት ሰንሰለት (GVC) ውስጥ ለመሳተፍ አስፈላጊ የሚያደረገው በሀገራት መካከል የሚኖረውን የትስስር ስራዎች ብቻ ሳይሆን ድርጅቶች የሚያቀርቧቸውን ምርቶች ተፈላጊነት እንዲያሳድግ ያደርጋል።

5.8 ዲጂታል ንግድ

የዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ማኑፈክቸሪንግ ሂደትን መቀየር ብቻ ሳይሆን የእቃዎች እና አገልግሎቶችን ግብይት ክፍያ ስርአትንም ይቀይራል። በዚህም የተነሳ የወደፊት የአለም ንግድ ማዕቀፍ በዲጂታል ንግድና ኢኮሜርስ (e-comerce) ከፍተኛ ተጽእኖ የሚያድርበት መሆኑ የማይቀር ነው። የዲጂታል ንግድ ጽንሰ ሀሳብ የእቃዎች እና አገልግሎቶች በዲጂታል መንገድ ንግድ ማከናወን በሸማቾች፣ በድርጅቶች እና በመንግስታት መካከል የምርት ልውውጥ እንዲከናወን የሚያደርግ ነው። ከዚህም መካከል እቃዎችና አገልግሎቶችን በዲጂታል ትእዛዝ መስጠት ድንበር ተሻገር የኤሌክትሮኒክስ ንግድ (e-comerce) እና እቃዎችና አገልግሎቶችን በዲጂታል መንገድ ለሸማቹ ማድረስ (አገልግሎቶች በአለም አቀፍ ደረጃ በኢንተርኔት ወይም በሌሎች መረቦች ማድረስን) ያካትታል። የዲጂታል ንግድ የግል ንግድ ተቋማት የንግድ ወጪያቸው እንዲቀንስ፣ ምርታማነታቸውንና ተወዳዳሪነታቸው እንዲያድግና በአዳዲስ የኤክስፖርት እድሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዲሁም የወጪ ምርትና አገልግሎቶችን በአይነት እንዲያሰፉ ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል። ስለሆነም የሀገራችን ተቋማት በሰፊ ገበያ ውስጥ ምርቶችን በዝቅተኛ ዋጋ እና በምቹ ሁኔታ በዲጂታል የተሳሰረ አለም አቀፍ ገበያ ላይ ከፍ ያለ ደረጃ እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል።

ሆኖም በዲጂታል ዘርፍ ለመሳተፍ እና ተጠቃሚ ለመሆን ለዲጂታል ስርዓት አመቺ የሆነ የንግድ ስርዓት እና ምቹ መሰረተ ልማት ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። የዲጂታል ስርዓት እና ንግድ በተለያዩ አስቻይ ተዋናዮች ተጽእኖ ሊደርስበት ይችላል። ከእነዚህም መካከል

መንግስታት፣ የልማት ማዕከላት፣ ፓርኮች፣ ዩኒቨርስቲዎች እንዲሁም አስቻይ አሰራሮች፣ ደንቦች፣ማበረታቻዎች፣ መሰረተ ልማት፣ ክህሎት የመሳሰሉትን ያካትታል። በቂ የሆነ እና በቀላሉ ሊገኝ የሚችል እንዲሁም አስተማማኝ የሆነ ትስስር እና ወደ ሰፊው ህዝብ መሰራጨቱ ሰዎችና ድርጅቶች በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ደረጃ በዲጂታል ኢኮኖሚ ያላቸው ተሳትፎ እንዲያድግ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል።

- በመንግስታት የሚፈረሙ የሁለትዮሽ፣ቀጣናዊ እና ዓለም አቀፍ ንግድና ኢንቨስትመንት ስምምነቶች ውስጥ ኢኮሜርስ እና የዲጂታል ንግድ ድንጋጌዎችን ማካተት ሀገራችን አስተማማኝ የሆነ እና የበለጠ የገበያ ድርሻ እንዲኖራት ያስችላታል። በዝቅተኛ የንግድ ወጪ ምርቶችን በአለም አቀፍ ገበያዎች ላይ ለመሸጥ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።
- በሁለትዮሽ፣ በአህጉራዊ እና በመንግስታት መካከል የመረጃ ልውውጥ ፍሰትን ማመቻቸት።
- የጉምሩክ አገልግሎቶች፣ ሰነዶች፣ ድንበር ተሻጋሪነት፣ የኤሌክትሮኒክስ ማመልከቻ እና የገቢና ወጪ ንግድ ፈቃድ አሰጣጥ መዘመን እና ዲጂታላይዝ መሆን የግል ዘርፍ ተወዳዳሪ እና በሁኔታዎች የማይለዋወጥ ጽኑ አቋም እንዲኖረው ያስችላል።
- የጋራ የሆኑ ድረ ገጾችን በመፍጠር ዝርዝር የገበያ መረጃዎችን ማስፈር በተለይም ተፈጻሚ ስለሆኑ ታሪፎች፣ የስሪት ሀገር ምንጭ መስፈርቶች፣ ከታሪፍ ውጪ ያሉ መሰናክሎች እና የገበያ ፍላጎት ለውጪ ንግድ ለተሰማሩ የንግዱ ማህበረሰብ ጠቃሚ ናቸው።

5.9 የሸማቾች ጥበቃ እና ፍትሃዊ ንግድ

የውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ ፖሊሲዎች የኢኮኖሚ እድገትን ለማስመዝገብ እና ሁሉን አቀፍ እና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማምጣት አስፈላጊ መሳሪያዎች ናቸው። ምቹ የንግድ ሁኔታን መፍጠር እና ለአምራቾች እና ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እድሎችን መስጠት ለተጠቃሚዎች ሰፊ የገበያ ምርጫ፣ ዝቅተኛ ዋጋ እና ጥራት ያለው ምርት አቅርቦትን ማረጋገጥ የበለጠ ጠቃሚ ነው። ሸማቾች መብቶቻቸው እንዲጠበቁ እና ውጤታማ የሆነ አለመግባባቶችን ለመፍታት እና ኪሳራን የሚያካክስ መፍትሄ በቀላሉ ማግኘት አለባቸው። የሸማቾች ጥበቃ ስራ ተጨባጭ እና ውጤታማ የሸማች መረጃ እና ትምህርት ይሰጣል፣ መለያ

መስጠትን እና ማስታወቂያን በተመለከተ ወሳኝ ጉዳዮችን ይሸፍናል። ለተገልጋዮች ጥበቃ የሚያደርግ እና ፍትሃዊ ንግድን የሚያበረታታ የንግድ ከባቢ ውጤታማ ስራ የሚሰሩ ገበያዎችን ለማፍራት እና የሸማቾችን ደህንነት ለማሻሻል ጠቃሚ ነው። ስለዚህ; የሚከተሉት የፖ/ሊሲ እርምጃዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ::

- የሸማቹን ጤና፣ ደህንነት እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ኢፍትሃዊ ድርጊቶች የመጠበቅ ግዴታ አለበት። የሸማች መብቶችን ተግባራዊ ለማድረግ፣ ግልጽ፣ ሁሉን አቀፍ እና የተጠናከረ የሸማቾች ጥበቃ ደንቦችን ይዘጋጃል።
- ለሁሉም ሸማቾች ተደራሽ የሆኑ ፈጣን መፍትሄዎችን ለማቅረብ መንግስት የተቋቋሙትን የአሰራር ዘዴዎች እና መሳሪያዎችን ያጠናክራል።
- ዝቅተኛ ጥራት፣ አደገኛ ይዘት እና ያልተገባ ምርት አያያዝ የሸማቹን ጤና እና ደህንነት አደጋ ላይ ይጥላል። በአገር ውስጥ ገበያ ላይ ጥራት የሌላቸው ምርቶችና አገልግሎቶች በተጠቃሚዎች ላይ የጤና ጠንቅ የሚፈጥሩ ለመከላከል እና የሸማቾችን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የደንበኞችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የህግ አፈፃፀም በሁሉም ደረጃ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ይደረጋል። ምርቶች ለሚሸጡበት ዓላማ ተስማሚ እንዲሆኑ ይደረጋል።
- ሸማቾች በመረጃ ላይ የተመሰረተ የግዢ ምርጫ ለማድረግ እና ለሸማቾች የውሸት ወይም የተሳሳተ መረጃ እንዳተላለፉ ይደረጋል፣ ትክክለኛ እና በቂ መረጃ እንዲያገኙ ይደረጋል።
- መንግስት የውድድር ደንቦችን ባወጣው መሰረት ማንኛውንም ጉዳት ለማስተካከልና ለማረም ውጤታማ የቁጥጥር ስራ ለመስራት ቁርጠኛ መሆን ይጠይቃል። በነጋዴዎች ወይም በቡድን የሚንቀሳቀሱ ነጋዴዎች ወይም አምራቾች ኢ-ፍትሃዊ የንግድ አሰራርን በመፍጠር አምራቹንም ሆነ ሸማቹን የሚጎዳ የንግድ ተግባር እንዳይፈፅሙ እንዲሁም የመንግስት የግዥ ስርዓት ግልፅነት ያለው አሰራርን በመተግበር ውድድርን በመጨመር ውጤታማ ለማድረግ ቅድሚያ ተሰጥቶ ይሰራል።
- አግባብነት ያለው የሸማቾች ጥበቃ ህግን ማጠናከር እና ማስማማት ፣በምርት ደህንነት ፣ጥራት መለኪያ ፣መለያ እና ማሸግ ላይ የቁጥጥር ማዕቀፎችን አፈፃፀም ማጠናከር ፣ በተጠቃሚዎች መብት ላይ ስርጭትን እና ግንዛቤን ማጎልበት እና በሸማቾች ደህንነት ጉዳዮች ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተቋማዊ አቅምን ለማጠናከር ይሰራል።

- የሀገር ውስጥ አምራቾችን ለመደገፍ በመንግስት ግዥዎች ውስጥ እንዲሳተፉ የሀገር ውስጥ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን አጠቃቀም እንዲተዋወቁ ይደረጋል።
- አዳዲስ ፈጠራዎች እና ሀሳቦች ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። ስለሆነም የአእምሯዊ ንብረት መብቶች ጥበቃ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርትን ለመጨመር አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እንዲፈጠሩ ያበረታታል፣ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ኢንቨስትመንትን ያነቃቃል፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ያመቻቻል እንዲሁም ተወዳዳሪነትን ያሻሽላል። ስለዚህ መንግሥት የብሔራዊ አእምሯዊ ንብረት መብቶች ሕግ አፈፃፀምን ያጠናክራል ፣ ከአእምሮአዊ ንብረት ጋር የተያያዙ ተዛማጅነት ያላቸውን ዓለም አቀፍ ሰነዶችን እና ምርምርን እና ልማትን ያከብራል ይደግፋል።

5.10 ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች

5.10.1 ስርዓተ ጾታ

በንግድ ፖሊሲው ውስጥ የፆታ እኩልነትን ማሻሻል ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገትን በማስመዝገብ ሀገራዊ ስትራቴጂክ የልማት ግቦችን (Goal 5 on Equality) ለማሳካት ያስችላል። ሀገራችን ከጾታ እኩልነት እና ከሴቶች እኩልነት መብት ጋር የተያያዙ በርካታ አለም አቀፍ ስምምነቶችን ያፀደቀች ሲሆን እነዚህን መርሆዎች በበርካታ የሀገር ውስጥ የዘርፍ ፖሊሲዎች ውስጥ በመርህ አካትታ በመስራት ላይ ትገኛለች።

ንግድና የሴቶች እኩልነትን በማስተሳሰር ኢትዮጵያ እኤአ በ2017 በተደረገው የዓለም ንግድ ድርጅት የሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ የሴቶችን ኢኮኖሚ ተጠቃሚነትየጋራ ውሳኔ ተቀብላለች ። በውሳኔው ላይ ሀገሮች የተስማሙት በሴቶች ላይ በመንግስት ግዥ የሚያጋጥሟቸውን የንግድ እንቅፋቶችን በተሻለ መንገድ ለመቅረፍ የሚያስችሉ መንገዶችን በመፈለግ እና የንግድ ስራ ፋይናንስ ለማገዝ እንዲሁም ተሳትፏቸውን ለማጠናከር ተስማምተዋል።።

ንግድ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትና አቅም በማጎልበት የጎላ ሚና አለው። ሴቶች ተዕእኖ ሊደርስባቸው የሚችለው እንደ ሥራ ፈጣሪነት፣ ተቀጣሪነት እና ሸማች ሴቶች በመሆናቸው ነው።

ሴቶች ሥራ ፈጣሪ በሆኑበት ዘርፍ ላይ በሴቶች በሚመሩ የንግድ ዘርፎች እና ምርቶች ላይ የተሻለ የታሪፍ ጥበቃ እንዲያገኙ በተመረጡ የንግድ ዘርፎች ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይገባል። በተጨማሪም የንግድ ወጪዎች መቀነስ በተለይ መደበኛ ባልሆኑ ነጋዴዎች ላይ በአብዛኛው

እነዚህ ስራዎች የሚከናወኑት በሴቶች ስለሆነ የወጪ ቅናሽ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና መብታቸው ወደሚያስጠብቁላቸው መደበኛ ስራ ዘርፎች ውስጥ እንዲሰማሩ ማድረግ ተገቢ ነው።

ሴቶች እንደ ሰራተኛ የንግድ መስፋፋት እና በሀገሪቱ ኢኮኖሚ አደረጃጀት የመንግስት ድርሻ በመቀነስ የግል ባለሀብቱ ተሳትፎ በማሳደግ በደመወዝ ተቀጥረው በሚሰሩ ሴቶች ቅጥር ላይ ተጽእኖ ሊፈጥር ይችላል። ሴቶች በእያንዳንዱ ዘርፍ በሚያደርጉት ተሳትፎ በቁጥር አሁን በሀገሪቱ ባለው ሁኔታ የሴቶችን የቅጥር ዋስትና ማሻሻል የንግድ ፖሊሲ ጉልህ ሚና አለው።

የንግድ መስፋፋት እና የመንግስት ድርሻ በመቀነስ የግል ባለሀብቱ ተሳትፎ በማሳደግ ሸማቾች ምርት በከፍተኛ መጠን እንዲያገኙ እና ዋጋቸው እንዲቀንስ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ሲሆን ይህም በሴቶች በሚተዳደሩ ወይም በሚመሩ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ተጠቃሚ ያደርጋል።

ስርዓተ ጾታን ያማከለ የንግድ ድርድሮችና ትግበራዎች የሚያረጋግጡት ሀገሪቱ የምታደርጋቸው ንግድ ስምምነቶች ሴቶችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ መሆኑን ማረጋገጥ የሥርዓተ-ፆታ ኢ-ፍትሃዊነት እንዳይቀጥል ያደርጋሉ። ሴት ተደራዳሪዎች ክአጋር አካላት ጋር በሚደረጉ ድርድሮች ላይ ተሳትፎ ማድረግ ይገባቸዋል።

5.10.2 የአየር ንብረት ለውጥ

ኢትዮጵያ ለከባቢ አየር ልቀትና ከባቢ አየር ለውጥ አነስተኛ አስተዋፅኦ ካደረጉ ሀገራት ተርታ ትጠቀሳለች። ድርቅ፣በየብስ እና በውሃ ላይ ያለው ሙቀት መጨመር፣የከባድ ዝናብ ክስተቶች ድግግሞሽ እና መጠን መጨመር እና የጎርፍ አደጋዎች እንዲሁም የአማካኝ የዝናብ መጠን መቀነስ ሁሉም በኢትዮጵያ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ተጽኖዎች ናቸው። አንዳንዶቹም ቀድመው በመከሰታቸው የኢኮኖሚ ተጽእኖ በሁሉም ዘርፍ የምርትና የንግድ ተወዳዳሪነት በማዳከም በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ተጽእኖ እያሳደረ ይገኛል። ስለዚህ ተዛማጅነት ያላቸው የአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ ሁሉንም ተጠቃሚና አሸናፊ ማድረግ የፖሊሲው ወሳኝ ጉዳይ ነው።

የኢትዮጵያ የአመራረት ስርዓት በአየር ንብረት ተጽእኖ ምክንያት ሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች በተለይ አካላዊ እና አስተዳደራዊ የአየር ጠባይ ስጋቶች ናቸው። በሀገር ውስጥ ሆነ በውጪ የአመራረት ሂደት ሲለዋወጥ የምርት ፍሰትና ብዛት እና መጠን ላይ ተጽዕኖው ይታያል።

በተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ማዕቀፍ (United Nations Framework Convention on Climate Change (UNFCCC)) መሰረት ኢትዮጵያ የማምረቻ ዘርፉን ለመደገፍ እና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር እንድትላመድ የገንዘብ ድጋፍ ያስፈልጋታል። ሀገራችን የምትተገብረው የንግድ ፖሊሲ የአየር ንብረት ዝግጁነትና የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃን እንዲሁም የአካባቢ፣ የብዝሀ ህይወት እና ሥነ-ምህዳር ጥበቃን ከግምት ውስጥ በማስገባት የማምረት አቅምን እና ምርታማነትን በማሳደግ በአለም ገበያ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ በትኩረት ይሰራል።

5.10.3 ስራና ሰራተኛ

በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት መሠረት የሠራተኞች መሠረታዊ መብቶችና የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ክልከላ ተደንግጓል። በተጨማሪም በ2011 አሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ከሰራተኛው ማህበረሰብ ጋር የተያያዙ የሰራተኛ መብቶች እና ግዴታዎች በዝርዝር ተቀምጧል። የስራ እድል በአብዛኛው በከተማ እና በመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ያተኮረ ነው። በተለይ በከተሞች ውስጥ ስራ የሌላቸው የህበረሰብ ክፍል ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሲሆን በዚህ ዘርፍ ውስጥ አብዛኛው ህዝብ ሴቶች እና ወጣቶች ናቸው.። ስለሆነም የንግድ ስርአቱ መጠናከር የስራ እድልን የሚፈጥር ይሆናል። የሰራተኞች የክህሎት ደረጃ ዝቅተኛ መሆን ቁልፍ ፈተና ሲሆን በአገሪቷ ንግድ ላይም ተፅዕኖ አለው። በአንድ ሀገር ውስጥ ያሉ የሰራተኞች የክህሎት ደረጃ በተመረቱ ምርቶች አይነት እና ስርጭት ላይ እንዲሁም የክፍያ ሚዛን ላይ ተጽእኖ አለው። ይህ ሁኔታ በአገሪቱ ብዙ የሰለጠኑ ሰራተኞች መገኘት ከፍተኛ ጥራት ያለው ምርት ትርጉም ባለው ደረጃ ለማምረት እንዲሁም ወደ ውጭ በመላክ የምርት ስብጥር እንዲስፋፋ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። በዚህ መሰረት የሰው ሃይል ክህሎት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማደግ አለበት እንዲሁም ቤተሰብ የተሻለ ገቢ ማግኘት እንዲችል በስፋት በንግድ ስራ መሰማራት የሚቻልበት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ይሰራል።

5.10.4 የአካል ጉዳተኛ አካታችነት

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ በርካታ ቁጥር ያላቸው አለም አቀፍ የልማት ድርጅቶች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የግሉ ዘርፍ እና መንግስት እና ሌሎች አካላት አካል ጉዳተኝነት በተለያዩ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ውስጥ እንደ ሌሎች የህብረተሰብ አካላት ታይተው መካተት እንዳለባቸው ታምኖበት እየተሰራ ይገኛል። አካል ጉዳተኞች ከሌሎች ዜጎች ጋር እኩል መብት አላቸው። እነዚህን መብቶች መሰረት ያደረጉ

አካሄዶች እንዲሁም አካል ጉዳተኞች ወደ ህብረተሰቡ ሙሉ በሙሉ እንዳይቀላቀሉ የሚከለክሉትን መሰናክሎች ማስወገድ ወሳኝ እና ለድህነት ቅነሳ እና ለበለጠ ሁሉን አቀፍ እና ቀጣይነት ያለው ልማት ትርጉም ያለው አስተዋፅዖ ያደርጋል።

ምንም እንኳን አካል ጉዳተኞች ምቹ በሆነ አካባቢ ውስጥ ብዙ ስራዎችን የመስራት እና ውጤታማ የመሆን ሁኔታ ቢኖርም ብዙ ጊዜ በስራ ላይ መድልዎ ይደርስባቸዋል.። ስለዚህ አካል ጉዳተኞችን በሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ማካተት አስፈላጊ ነው። አዋጆችን እና ደንቦችን በማውጣት ሂደት አካል ጉዳተኞችን ማሳተፍ እና ለነሱ ተስማሚ እንዲሆኑ ማድረግ እና ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠር እና መድሎዎችን መከላከል ይገባል። በተጨማሪ የመንግስት የግዥ ደንቦች በአካል ጉዳተኞች ባለቤትነት የተያዙ የንግድ ድርጅቶች የሚሳተፉበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ በዓለም አቀፍ ገበያዎች ላይ ያላቸውን ተሳትፎ እንዲያድግ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል።

5.10.5 ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች

ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ሥራ በመፍጠር ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። እንዲሁም የሴቶችን ሥራ ፈጣሪነት እና የልማት ስራ ተሳትፏቸውን በማስፋትና በማስተዋወቅ የላቀ ሚና አለው። ሆኖም ግን እነዚህ ኢንተርፕራይዞች በአለም አቀፍ ንግድ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ትንሽ ነው። በተለይም ኢንተርፕራይዞቹ ወደ ውጭ የሚላኩ እና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች ድርሻ ከቁጥራቸው እና ለስራ ስምሪት ከሚያደርጉት አስተዋፅዖ አንፃር አነስተኛ ነው። በአለም አቀፍ ንግድ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ እንዲሆን ከሚያደርጉት ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ ከፍተኛ የንግድ ወጪ መብዛት ነው። ወደ ውጭ የሚላኩ አብዛኞቹ የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ምርት ከትላልቅ የንግድ ድርጅቶች ጋር ተመሳሳይ የንግድ እንቅፋቶች ያጋጥማቸዋል። ሆኖም ኢንተርፕራይዞች አብዛኛውን ጊዜ አነስተኛ ካፒታል ስላላቸው የውጭ ገበያ ለማግኘት መቸገር እና ለውስብስብ የቁጥጥር መስፈርቶች ምላሽ የመስጠት አቅማቸው አናሳ ነው። ኢንተርፕራይዞች በአለምአቀፍ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ እንዲሳተፉ የሚያበረታቱ ፖሊሲዎች ከውጭ ገበያ ጋር በተያያዘ ቴክኒካል እገዛን የሚሰጡ እና ከንግድ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለመፍታት የቁጥጥር መስፈርቶችን እንዴት ማሟላት እንደሚችሉ የሚያሳልጡ ስራዎች እና የሚያግዙ ድርጅቶች እንዲጠናከሩ ይደረጋል። በተጨማሪም ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስራ በሀገር ውስጥ እና

በአለም አቀፍ የንግድ ተሳትፎ ውስጥ ተዛማጅ የንግድ ወጪዎችን በመቀነስ ኢንተርፕራይዞችን እንዲረዱ በትኩረት ይሰራል።

6 የፖሊሲው ቁልፍ ውጤቶች

የዚህ ንግድ ፖሊሲ ዋነኛ ዓላማ ሀገራችን እያስመዘገበች ያለችውን ፈጣን፣ መሰረተ ሰፊ እና የአየር ንብረት ለውጥን ያገናዘበ የኢኮኖሚ እድገት በማስቀጠል እና በአህጉርና በአለም አቀፍ ደረጃ ያላትን የንግድ ልውውጥ በማስፋት በአጭር ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ እንድትሰለፍ ማስቻል ነው። በኢትዮጵያ ንግድን ለማስፋፋት እና ኤክስፖርትን ለማሳደግ ያለው አማራጭ የምርት ሂደትን፣ ምርታማነትን፣ ውጤታማነትን፣ አቅምን እና ተወዳዳሪነትን በመጨመር የወጪ ንግድን ማሳደግ ነው። የግዥ ወይም የሽያጭ ዋጋን ከፍ ወይም ዝቅ አድርጎ ማስመዝገብ፣ ዝቅተኛ የጥራት ደረጃ፣ የሎጀስቲክስ አለመጣጣም፣ የህጎች በየጊዜው መለዋወጥ በኢትዮጵያ ንግድ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሲፈጥሩ ቆይተዋል። ስለዚህ ይህ የንግድ ፖሊሲ የኤክስፖርት ገቢን ለመጨመር፣ የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለማሳደግ፣ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የእውቀት ሽግግር ለማምጣት እና ኢትዮጵያን በአለም አቀፍ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ለማካተት ነው። ይህም ጠንካራ፣ ዘርፈ ብዙ፣ አስተማማኝ እና ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ ለመገንባት እና የአፍሪካ የኢንቨስትመንት ማእከል ለማድረግ ዋና ምሰሶ ነው። ፖሊሲው የንግድና የግብዓት ወጪዎችን በመቀነስ እንዲሁም የፋይናንስ ግኝትን በኢንቨስትመንት በማገዝ፣ እሴት የተጨመረባቸውን ምርቶች ድርሻ በማሳደግ፤ በሀገር ውስጥ፣ በአህጉራዊ እና በአለም አቀፍ እሴት ሰንሰለት ውስጥ በመግባትና በማጠናከር በተለይ ለሀገራችን ስልታዊ ጠቀሜታ ባላቸው ዘርፎች የግብርና ንግድ ስራ (agri-business) እና ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ዘርፎች ላይ በመሳተፍ ተወዳዳሪነትን ሊያሳድግ ይችላል። ይህም የሁሉም ባለድሻ አካላት አስተዋጽኦ በማቀናጀት እንዲሁም በኢንዱስትሪው እና በኢንቨስተሮች መካከል ትስስር በማጠናከር የልማትና ድህነት ቅነሳ መንታ ዓላማዎችን ለማሳካት ጥቅም ላይ ይውላል።

የንግድ ፖሊሲው በሀገራዊ ልማት ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ማለትም ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፣ የኤክስፖርት ዳይቨርስፊኬሽንን ማስፋፋት፣ ፈጠራ እና የውጭ ንግድን ማበረታታት፣ የንግድ እድሎችን ማስፋት እና ከድንበር ወዲህ፣ በድንበር ላይ እና ከድንበር ወዲያ ያሉትን መሰናክሎች ማስወገድን አጣምሮ የያዘ ነው። ከሀገር ውስጥ ንግድ አስፈላጊነት አንፃር ሲታይ ፖሊሲው በሸማቾች እና በአምራቾች መካከል ያለው ሚዛን ብቻ ሳይሆን

በኤክስፖርት ላይ ያተኮሩ ድርጅቶችና እና ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚያመርቱ ድርጅቶች ፍላጎት መካከል ያለውን ሚዛን ለማስጠበቅ ያለመ ነው።

የገንዘብ፣ የፊስካል፣ የውጪ እና ኢንዱስትሪ ፖሊሲዎች ገንዘብ እንዲመደብና ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ እንዲሁም የስራ እድልን በመፍጠር ሚዛን በመጠበቅ አገራችንን በባለብዙ ወገን የንግድ ስርዓት (multilateral trading system) ውስጥ ለማስገባት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። ስለዚህ የዚህ ንግድ ፖሊሲ ዝግጅት አላማ ሊሳካ የሚችለው በርካታ ሚኒስቴር መ/ቤቶች እና ተቋማት በቅንጅት ሲሰሩ ነው። ለምሳሌ የኢንዱስትሪ ፖሊሲው የኢንዱስትሪ ልማትን በማስፋፋት መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ለውጥ እዲመጣ ይሰራል። በኢንዱስትሪ መዋቅር እና በትስስር ሂደቶች ላይ በማተኮር ጠንካራ መስተጋብር እንዲኖር ያደርጋል። ይህ ሊሳካ የሚችለው ሌሎች የደረሱበት ለመድረስ የሚያስችል የኢንዱስትሪ ልማትን በማፋጠን እያደገ የሚሄደውን ህዝብ መመገብ እና ሀገራችንን የአፍሪካ የማኑፋክቸሪንግ ማእከል በማድረግ ነው።

በዚህ የንግድ ፖሊሲ ውስጥ የተቀመጡትን አላማዎች ስኬት የሚያግዝና የንግድ ስርአቱን ለማሻሻል የሚረዳ አጠቃላይ ማዕቀፍ የያዘ የ10 ዓመት መሪ የልማት እቅድ ተቀርጿል። በዚህ ረገድ ከዚህ ፖሊሲ የሚጠበቁ ቁልፍ ውጤቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፦

- የሀገር ውስጥ ንግድን ማዘመን፤
- የኤክስፖርት ምርቶችን ብዛት፣ አይነትና እና ጥራት ማሻሻል፤
- ተወዳዳሪ፣ ዘመናዊ እና ቀልጣፋ የንግድ ስርኣት መፍጠር፤
- የገበያ ትስስርን በማጠናከር የውጭ ምንዛሬ ገቢን ማሳደግ፤
- የአለም ንግድ ድርጅት ተሳትፎ ሂደትን ማጠናቀቅና ወደ ትግበራ ማስገባት፤
- የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት አባልነትን አሟጦ መጠቀም፤ እና
- የሸማቾች ጥበቃ እና ፍትሃዊ የገበያ ውድድርን ማረጋገጥ ናቸው።

7 ፖሊሲ የማውጣት ስልጣን

ይህን የንግድ ፖሊሲ የማውጣት ስልጣን የኢፌዲሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው።

8 የፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስልት

ፖሊሲው የሀገራዊ ልማት እቅድ ግቦች ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮችን ያካተተ ሲሆን በዋነኝነት ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፣ የኤክስፖርት ምርቶችን ማስፋፋት፣ ፈጠራና ለሁሉም ክፍት የሆነ ነጻ የንግድ ስርአትን ማበረታታ፣ የንግድ እድሎችን ማስፋትና ንግድ በማሳለጥ ከድንበር በፊት፣ በድንበር ላይ እና ከድንበር በኋላ ያሉ መሰናክሎችን ማስወገድ የሚሉትን የሚጨምር ነው። ስለዚህ የፖሊሲ ትግበራው ጉዳዮቹ የሚመለከታቸው ተቋማት የሚያካትት መሆን አለበት። የትግበራው አቀራረብ የአጭር ፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ አሰራር እንደሚከተለው ቀርቧል።

- **የአጭር ጊዜ፡** በአጭር ጊዜ ውስጥ የትግበራው ሂደት የሚያተኩረው የንግድ ፖሊሲን ለሚያስተገብሩ ተቋማት አቅም መገንባት ነው። ስኬታማ የሆነ የንግድ ፖሊሲ ትግበራ በቀጥታ የበርካታ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ባለድርሻ አካላትን ሚና በመለየት የልማት ግቦች የማሳካት ዓላማ መያዝ፣ የአጋር አካላት ተሳትፎ እና አካታችነትን የሚጠይቅ ነው። ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ አስፈጻሚ የመንግስት አካላት ፖሊሲውን የማስፈጸምና የመከታተል፤ የንግዱ ማህበረሰብ በተቀመጡ መለኪያዎች መሰረት የመተግበር እንዲሁም የሲቪል ማህበረሰብና የምርምር ተቋማት የሌሎቹን የማህረሰብ ክፍሎች ፍላጎት በጥናትና በአድቮከሲ ስራዎች ፓሊሲዎችን እንዲያውቁዋቸው የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው።
- **የመካከለኛ ጊዜ፡** በመካከለኛ ጊዜ ውስጥ ትግበራው የሚያተኩረው በንግድና ንግድ ነክ በሆኑ ፖሊሲዎች እንዲሁም የሰው አቅም መገንባት ላይ ነው። ንግድን ሊበራላይዝ በማድረግ የገበያ እድል በመፍጠር የዓለም ንግድ ድርጅት መቀላቀል ነው።
- **የረጅም ጊዜ፡** እነዚህ የልማት መር ዋና ዋና የንግድ ፖሊሲ መዋቅሮች በትኩረት መስራት ያለባቸው ንግድ ላይ የተመሰረተ የምርትና አገልግሎት አቅርቦትና የአመራረት አቅምን ማሳደግ፣ ድርጅቶች በአለም አቀፍ የእሴት ሰንሰለት ላይ ተሳስረው እንዲሳተፉ ማድረግ፣ ከፍተኛ እሴት የተጨመረባቸውን ለኤክስፖርት ንግድ የሚውሉ ምርቶችን ማስፋፋት እንዲሁም የውጪ ንግድ እና የምርቶችን አይነት የሚጨምሩ ውጤታማ ኢንቨስትመንት በማድረግ በእወቀት የሚመራ የኢኮኖሚ ስርዓት በቀጣይ መገንባት የረጅም ጊዜ እቅድ ነው።

ለንግድ ፖሊሲ አተገባበር ስኬት ትግበራ በዋነኝነት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በንግድ ፖሊሲው ውስጥ ቀረጻና አፈፃፀም ላይ ተሳትፎ በሚያደርጉ አጋር አካላት ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ ነው። በተጨማሪም የንግድ ፖሊሲ ቀረጻና ማስፈጸም ላይ ኃላፊነት ያለባቸውን አካላት በግልጽ መለየትና ማወቅ እንዲሁም ተያያዥ አጋር አካላትን መለየት እንዲሁም የሚሳተፉበትን ደንብ ማዘጋጀት፣ ሌሎች ህጎችን መፈተሽ እና ማስፈፀሚያ የልማት ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት ወሳኝ ነው።

8.1 ፈፃሚ ተቋማት

ምንም እንኳን አዋጁ በግልጽ ለንግድ ፖሊሲ ቀረጻ ዋነኛ ኃላፊነት ያለበት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ቢሆንም ሌሎችም ተቋማት በኢትዮጵያ ንግድ ፖሊሲ ቀረጻና ትግበራ ላይ ኃላፊነት አለባቸው። የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የውጪ ንግድ ግንኙነቶችን ይመሰርታል፣ የንግድ ስምምነቶችን ይፈራረማል፤ ያፀድቃል እንዲሁም ይተገብራል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም የሀገሪቱን የውጪ ንግድ እና ቱሪዝም ለማስፋፋት፣ የውጪ ኢንቨስተሮችን መለየትና መሳብ፣ መፈለግ፣ የቴክኖሎጂ ምርጫና ሽግግር ማድረግ፣ ከውጪ ምንጮች የፋይናንስና ቴክኒክ ድጋፎች እንዲመጡ ለማድረግ በዲፕሎማሲ ዘርፉ የመንግስት አስፈፃሚ አካል ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነት አለበት"። የፕላን እና ልማት ሚኒስቴር በበኩሉ "ቁጠባ፣ ኢንቨስትመንት እና የኢምፖርትና የኤክስፖርት የኢኮኖሚ ግቦችን በማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ያዘጋጃል። በተጨማሪም የክልል የሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያቤቶች እና ለንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ፖሊሲውን በማስፈፀም የላቀ ድርሻ አላቸው።

ይህ ሁሉ የሚያሳየው ሌሎች የመንግስት አካላት በሙሉ ለንግድ ፖሊሲው ትግበራ እና/ወይም ፖሊሲ ቀረጻ ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር ተባብረው የመስራት ኃላፊነት ያለባቸው ከመሆኑ በተጨማሪ የሚከተሉት ጉዳዮችም በትኩረት መተግበር አለባቸው።

በሚኒስቴር መ/ቤቶችና ድርጅቶች መካከል ያለውን ትብብር ማሻሻል፦

የኢትዮጵያ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በፖሊሲ ቀረጻ ከዘመናዊ አለም አቀፍ ንግድ ጋር የመተሳሰር፣ ከውጪ ጉዳይ ፖሊሲ፣ የፊሲካል ፖሊሲ ጋር በተያያዘ ኃላፊነት ያለበት ተቋም ነው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሌሎች በርካታ የመንግስት ተቋማት በንግድ ፖሊሲ ቀረጻ ላይ ወይንም በትግበራው ላይ ተሳትፎ ያደርጋሉ። ስለዚህ እነርሱን የፖሊሲ ቀረጻ ተግባር ላይ ሲሳተፉ ካለባቸው ኃላፊነት አንጻር በተደጋጋሚ ውይይቶች ማደረግ

ያስፈልጋቸዋል። ይህም ምናልባት አሁን በተግባር ላይ ያለውን በሚኒስቴር መ/ቤቶች ያለውን የአሰራር ሂደት እና ትብብር ስነ ስርዓት እንዲሁም የሰው ሀብትና የፋይናንስ ድንጋጌዎችን ማሻሻል ሊጠይቅ ይችላል። በተጨማሪም ዋነኛ ግባቸው ከንግድ ጋር ያልተገናኙ ሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች/ኤጀንሲዎች ግልጽ የሆነ ኃላፊነት እና ተጠያቂ የሚሆኑበት አሰራር መመቻቸት ይኖርበታል።

የኢምባሲዎችን እና የሀገሪቱን የውጪ ሚሲዎኖችን መጠቀም፦ በብዙ ሀገሮች የውጪ ኢምባሲዎቻቸውን እና ጽ/ቤታቸውን ለድርጅቶቻቸው ስለ አለም አቀፍ ንግድ ስርአት ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና በቂ መረጃ እንዲያገኙና የንግድ እድሎችን ለመፍጠር እንደሚጠቀሙበት ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይህ ሊተገበር የሚችለው በኢምባሲዎች ውስጥ ንግድና ኢንቨስትመንት የሚያስፋፉ ጽ/ቤቶችን በመመስረት ነው። ከኤክስፖርተሮች እና ከኢምባሲ ባለስልጣናት ጋር ቀጥተኛ ትስስር በመፍጠርና በመገናኘት የኢትዮጵያ ኢምባሲዎች እና ሌሎች ሚሲዮኖች ለኢትዮጵያ ንግድ ዘርፎች የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎችን የማስፋፋት እንዲሁም የውጪ ንግድ ኢንቨስትመንት ለማግኘት የንግድ ባዘሮችና ትዕይንቶችን በማዘጋጀት ማስተዋወቅ ይገባል።

ተጨማሪ አጋር አካላትና ሚናዎቻቸው፦ የንግድ ፖሊሲ የቀረጻ ሂደት ትግበራና ቁጥጥር ስራ በርካታ አጋር አካላትን የሚያሳትፉ ሂደቶች ናቸው። እነሱም የንግድ ድርጅቶች፣ ሰራተኞች፣ ኢንዱስትሪዎች፣ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ፣ ግብርና፣ አገልግሎት ሰጪ ኢንዱስትሪዎች፣ ቸርቻሪዎች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የአካባቢና የጥበቃ ድርጅቶች እና የሸማች ጥቅም የሚያስከብሩ ሲቪል ማህበራት፣ ሚዲያዎች እና የምርምር ተቋማት ይገኙበታል። ለንግድ ፖሊሲው ስኬታማነት አጋር አካላት በፖሊሲዎች ድርድርና ትግበራ ላይ እንዲሳትፉ ማድረግ ወሳኝ ነው። በኢትዮጵያ የንግድ ፖሊሲ ትግበራ ላይ አጋር አካላት ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲሻሻል ጥረት ይደረጋል።

8.2 የህግ ማእቀፍ

በስራ ላይ ያሉ አዋጆች እና ደንቦች በዝርዝር መታየት እና መከለስ የሚኖሩባቸው ሲሆን ከእነዚህም መሀል የሚከተሉት ይገኙበታል፡

- የንግድ ምክር ቤትና የዘርፍ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/1995 (ማሻሻያ)
- የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/206 (ማሻሻያ)
- የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ (ማሻሻያ)

- የቅባት እህሎችና የጥራጥሬ ማርኬቲንግ ደንብ (ማሻሻያ)
- አጋር አካላት እንዴት በይፋ ማሳተፍ እንደሚቻል መመሪያ ማዘጋጀት፡ አጋር አካላትን ማቋቋም እንዲሁም ባለሙያዎችን የሚያደረጁ ንኡሳን ኮሚቴዎችን እንዲያቋቁሙ መፍቀድ ወሳኝ ነው።

8.3 የልማት ፕሮግራሞች

ከዚህ የንግድ ፖሊሲ ትግበራ የሚጠበቁ ሰባት ቁልፍ ውጤቶች አሉ። እነዚህ ቁልፍ የፖሊሲ ውጤቶችን ለማሳከት የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር መደበኛ በጀት የሚጠቀም ቢሆንም ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ሚጠይቁ አዳዲስ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ማቋቋም፣ ሌሎች መሰረተ ልማቶችን መገንባት፣ መሰረታዊ ጥትና ምርምር በማድረግ የድርድር ሰነዶችን ማዘጋጀት፣ የሰው ሃይል አቅም ግንባታ እንዲሁም ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው የሀገሪቱን ወጪ ምርቶች ለማስተዋወቅ ኢግዚቢሽኖችን እና ኤክስፖዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በመሆኑም እነዚህ ስራዎች በተነጻጻሪነት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚጠይቁ በመሆኑ የሚከተሉት የልማት ፕሮግራሞች ተለይተዋል።

ውጤት 1፡ የዘመነ የሀገር ውስጠ ንግድ

በዚህ ንግድ ፖሊሲ ንግድን ለማዘመን ሶስት ፕሮግራሞችና አምስት ንኡስ ፕሮግራሞች ተዘጋጅተዋል።

9.3.1 የሀገር ውስጥ ንግድ ማመቻቸት ፕሮግራም

- የገበያ መረጃ ስርአት ግንባታ ንዑስ ፕሮግራም፡ ተአማኒ እና ወቅታዊ የገበያ መረጃ እና ዝርዝር ስታትስቲካል መረጃዎችን የማዘጋጀት ስራ።
- የገበያ ትስስር ስርአት ንኡስ ፕሮግራም፡ በክልሎች መካከል ያለውን የግብርና ኢንደስትሪ ምርቶች አቅርቦት እና ፍላጎት ትስስር ስርአት ለመገንባት ነው።

9.3.2 የንግድ ስራ መጀመር እና ማከናወን ምቹነት ማሻሻያ ፕሮግራም

- የኢ-ንግድ ስርአት ልማት ንዑስ ፕሮግራም
- ለንግዱ ማህበረሰብ የአቅም ግንባታ ንዑስ ፕሮግራም
- የንግድ አሰራር ጥናትና ምርምር ንዑስ ፕሮግራም፡- በንግድ ስራ መጀመር እና ማከናወን ለማሻሻል የሚያስችል ምርምርና ጥናት በማድረግ ምክረ ሀሳቦችን ማቅረብ

ሀገሪቱ ተወዳዳሪ እና ኢንቨስትመንትን የሚስብ አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው ደረጃ እንዲኖራት ያግዛል።

እነዚህ ዋና ዋና እና ንዑስ ፕሮግራሞች በዋነኝነት የሚከናወኑት በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በተጨማሪም በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አማካኝነት በሚደረግ የቴክኒክ እገዛ እና የተገነባውን የቴክኖሎጂ ስርዓት ማረጋገጫ በመስጠት ይሰራሉ።

ውጤት 2፡ **በአይነት፣ በመጠን እና በጥራት ያደገ የኤክስፖርት ምርት**

የኤክስፖርት ምርቶችን በአይነት፣ በመጠን እና በጥራት ለመጨመር ዘመናዊ የምርት ግብይት ስርአት መገንባት እና የግል ድርጅቶች በአህጉራዊ እና በዓለም አቀፍ የምረት ሰንሰለት ውስጥ ማሳተፍ የሚሉ የልማት ፕሮግራሞች ተይዘዋል።

9.3.3 ዘመናዊ የምርት ግብይት ስርአት ማበልጸግ ፕሮግራም

- ዘመናዊ የወጪ ምርቶች ገበያ መረጃ ስርአት ግንባታ ንዑስ ፕሮግራም፡- ለወጪ ምርቶች አስተማማኝ እና ተደራሽ የሆነ የምርትና የገበያ መረጃ ስርአት ለመገንባት ነው።
- የኤሌክትሮኒክ ግብይት ሲስተም ማበልጸግ ንዑስ ፕሮግራም፡- የወጪ ምርአችን አቅራቢ እና ላኪ በአካል ሳይገናኙ በኤሌክትሮኒክ ሲስተም መገበያየት የሚችሉበት ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክ ገበያ ስርአት ለመገንባት ነው።
- የግብይት ተሳታፊዎች አቅም ግንባታ ንዑስ ፕሮግራም፡- የኤሌክትሮኒክ ገበያ ተቆጣጣሪዎች እና ሌሎች ተዋናዮች (ሻጮች፣ ገዢዎች፣ የፋይናንስ ተቋማት እና ኦዲተሮች) አቅም ለመገንባት።
- ዘመናዊ የኤክስፖርት ምርት ውል እና የአስተዳደር ሲስተሞችን ማበልጸግ ንዑስ ፕሮግራም
- የመጋዘን ደረሰኝ ስርአት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

9.3.4 የተቀናጀ የግል ድርጅቶች በአህጉራዊ እና በአለም አቀፍ እሴት ሰንሰለት ተሳትፎ ማሳደግ ፕሮግራም

በእሴት ሰንሰለት ውስጥ ለማሳተፍ ያሉ እድሎችን ለመለየት የሚያስችሉ ምርምሮችና ጥናት ስራዎችን መስራት እና ግል ተቋማትን በብቃት እንዲሳተፉ የሚያስችል የአቅም ግንባታ ስራ ለመስራት ነው፡፡

አብዛኞቹ ፕሮግራሞችና ንኡስ ፕሮግራሞች የሚተገበሩት በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አማካኝነት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የኤሌክትሮኒክስ ግብይት መሰረተ ልማቶችን የማበልጸግ እንዲሁም ግብርና ሚኒስቴር የመጋዘን ደረሰኝ ስርአት እንዲተገበር ኃላፊነት ያለበት ሲሆን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የግል ተቋማት አህጉራዊና አለም አቀፍ የእሴት ሰንሰለት ተግባራት እንዲሳተፉ የማድረግ ሚና የሚጫወት ሲሆን የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተገነባው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ትክክለኝነትን እና ደህንነትን የማስጠበቅ ስራዎችን ይሰራሉ፡፡

ውጤት 3፡ ተወዳዳሪ፣ ፍትሃዊ እና ቀልጣፋ የንግድ ስርአት

ተወዳዳሪ፣ ፍትሃዊ እና ቀልጣፋ የንግድ ስርአት በሀገሪቱ ውስጥ እዉን ለማድረግ የሚከተሉት ሶስት የልማት ፕሮግራሞች ማለትም የሸማቾች ጥበቃ፣ የመንግስት እና ግል ድርጅቶች አጋርነት እና የገበያ ተደራሽነት ተለይተዋል፡፡

9.3.5 የሸማቾች ጥበቃ ፕሮግራም፡- ይህ ፕሮጋራም ትኩረት የሚያደርገው በዋነኝነት በተለያዩ መንገዶች በኤሌክትሮኒክስ እና በህትመት መገናኛ ብዙሀን በመጠቀም የሸማቾችን ግንዛቤ ማሳደግ ነው፡፡

9.3.6 የመንግስት እና ግል ድርጅቶች አጋርነት ፕሮግራም፡- ፕሮግራሙ የሚያተኩረው የንግድ ምክር ቤት፣ የሸማቾች ጥበቃ ማህበራትን እና የምርት ገበያ ተሳታፊ ማህበራትን አቅም በመገንባት የንግድ ስርዓቱ ፍትሃዊ፣ ተወዳዳሪ እና ቀልጣፋ እንዲሆን በማድረግ ላይ ነው፡፡

9.3.7 የሀገር ውስጥ ገበያ ልማት ማሳለጥ ፕሮግራም

- የሰንበት ገበያ ማስፋፊያ ንዑስ ፕሮግራም፡- የከተማ ነዋሪው እና ሸማቹ መሰረታዊ የምግብ ፍጆታን የሚሸምትበትን በሚችላቸው የሰንበት ገበያ በማስፋፋት አምራቹ እና ሸማቹ በቀላሉ የሚገናኙበት ሁኔታ መፍጠር እንዲሁም በቀላሉ ሊበላሹ ለሚችሉ ምርቶች አመቺ የሆኑ መጋዘኖችን እና

መሰረተ ልማቶችን በማስፋፋት ለሸማቹ አመቺና ደህንነቱ የተጠበቀ ምርት ማቅረብ፡፡

ሁሉም ፕሮግራሞችና ንዑስ ፕሮግራሞች የሚከናወኑት በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አማካኝነት ሲሆን የገበያ ማስፋፋትና ተደራሽነት ፕሮግራም ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር፣ ከከተሞች አስተዳደርና ከግል ኢንቨስተሮች ጋር በመተባበር ነው፡፡

ውጤት 4፡ ያደገ የወጪ ምንዛሬ ገቢ

የንግድ ፖሊሲ ትግበራ ውጤት ከሆኑት መሀከል አንደኛው የወጪ ምርቶች እና አገልግሎቶች በአይነት፣ በጥራት እና ብዛት በማሳደግ እንዲሁም የመዳረሻ ሀገሮችን ቁጥር በመጨመር የውጪ ምንዛሬን ገቢ ማሳደግ ነው፡፡ እነዚህን ቁልፍ ውጤቶች በተመለከተ ሁለት ፕሮግራሞችና ሶስት ንዑስ ፕሮግራሞች ተለይተዋል፡፡

9.3.8 የወጪ ምርት ገበያ ማስተዋወቅ እና ጥናት ፕሮግራም

- የወጪ ምርቶች ኢግዚቢሽን እና ኤክስፖ ዝግጅት ንዑስ ፕሮግራም፡- የውጪ ቱሪስቶች በሚገኙባቸው በሀገር ውስጥ የተለያዩ ቦታዎች ላይ የኤክስፖርት ምርቶች የሚታዩባቸው ኢግዚቢሽኖችን ማዘጋጀት፡፡
- የዲጅታል ገበያ ስርአት ልማት ንዑስ ፕሮግራም

ሁሉም ፕሮግራሞችና ንኡስ ፕሮግራሞች በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ባለቤትነት ነው፡፡

ውጤት 5፡ የላቀ አለማቀፋዊ እና ቀጣናዊ ትስስር

9.3.9 ቀጠናዊ ትስስር ማሳለጥ ፕሮግራም

ከሀገሮች ጋር ጠንካራ ትስስር መፍጠር ጠቀሜታው ለኤክስፖርት ንግዱ ብቻ አይደለም ይልቁንም ሰላማዊ እና የዲፕሎማሲ ግንኙነት በመመስረት በክልሉ አባል ሀገሮች መካከል ትብብር እንዲሰፍን ማድረግ ነው፡፡ ይህንን ቁልፍ ውጤት ለማሳካት የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም እና ፍላጎት በሚያከብር ሁኔታ ቀጣናዊ ትስስር በመፍጠር በአፍሪካ ነጻ የንግድ ስምምነት ውስጥ ድርድር እንዲከናወን ማድረግ፣ ከኮሜሳ ሀገሮች ጋር የተደረጉ የንግድ ስምምነቶችን በማጥናት የስምምነት መነሻዎችን ማዘጋጀት በሀገሪቱ ጥቅም ላይ ተመስርቶ እና የድንበር ገበያ መሰረተ ልማት በማበልጸግ እና ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ስምምነት

በመፈራረም ከድንበር ገበያ የአካባቢው ነዋሪዎች እና ሀገራቱ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

9.3.10 የወጪ ምርት መዳረሻ አገራት ጥናትና ድርድር ሰነድ ዝግጅት ፕሮግራም

- የሁለትዮሽ፣የቀጠናዊና የባለብዙ ዘርፍ ስምምነቶች ጥናትና ምርምር ስራ እና የስምምነት ሰነዶች ዝግጅት ንዑስ ፕሮግራም፡- የኢትዮጵያ የወጪ ምርቶች እና አገልግሎቶች በአህጉራዊ እና አለም አቀፍ ገበያዎች ላይ አመቺ የሆነ አቅርቦት እንዲኖራቸው ማስቻል ሲሆን የድርድር ሰነዶች ማዘጋጀት ደግሞ በመንግስታት እና በበርካታ መንግስታት የንግድ ስምምነቶች ላይ የሀገሪቱን ጥቅምና ፍላጎት ላይ የሚያስከብር የድርድር ሀሳብ ለማቅረብ ነው፡፡
- የአለም ንግድ ድርጅት አባልነት ድርድርን ማጠናቀቅ ንዑስ ፕሮግራም

ፕሮግራሙ የሚከናወነው በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር እንዲሁም ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ነው፡፡

8.4 የፖሊሲ ክትትልና ግምገማ

8.4.1 የክትትል እና ግምገማ ስርዓት

መንግስት በተለያዩ ጊዜያት ሰፊና ጥልቀት ያላቸው የንግድና ኢንቬስትመንት ስምምነቶችን አድርጓል፡፡ እነዚህ የተፈረሙ የንግድ ስምምነቶች እና ፖሊሲዎች ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ለማረጋገጥ አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ ማሻሻያ የሚደረግበት የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተፈረሙ የንግድ ስምምነቶችንና ፖሊሲዎችን አፈጻጸም በየጊዜው በተደራጀ የክትትልና ግምገማ ስርዓት መተግበር በሂደት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን በመቅረፍ ከስምምነቶቹ የሚገኘውን የንግዱን ማህበረሰብ፣ የሰራተኞችና የሸማቹን ተጠቃሚነት ማሳደግ የሚያስችል የድርድር ሀሳቦችን ለማመንጨት ይረዳል፡፡

የንግድ ስምምነቶችን እና ፖሊሲዎችን መከታተል ማለት ፖሊሲዎቹ እና ስምምነቶቹ በምን ያህል ደረጃ በትክክል እየተተገበሩ መሆኑን መለየት ነው፡፡ በሌላ በኩል ግምገማ ማለት የተፈረሙ የንግድ ስምምነቶችና ፖሊሲዎች ያስገኟቸውን ተጽእኖ እና የተመዘገቡ ውጤቶችን መመርመር ወይም መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም የንግድ ስምምነቶች እና

ፖሊሲዎች የተቀመጠላቸውን አላማና ግብ በማሳከት ለንግዱ ማህበረሰብ፣ ለሸማቾች እና ለሰራተኞች ያስገኙትን ጥቅም መመርመር አስፈላጊ ይሆናል።

የስምምነቶችና ፖሊሲዎች ያሳደሩትን ተጽዕኖ ለመከታተተልና ለመገምገም የሚያስችሉ ዘዴዎችን ማዘጋጀት በመጀመሪያ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ቢሆንም በሂደት ግን በተዘጋጀው የክትትልና ግምገማ ሞዴል መጠነኛ ማስተካከያዎችን ብቻ በማድረግ ወደፊት በሚደረጉ በርካታ ስምምነቶችና ፖሊሲዎች ላይ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል።

የንግድ ስምምነቶችና ፖሊሲዎች ክትትልና ግምገማ ስፋትና ጥልቀት በአጠቃላይ መርሆዎች ላይ የሚመሰረት ሲሆን በተለይም ስምምነቱ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል። ለምሳሌ አንዳንድ ስምምነቶች ከአንድ ሀገር ጋር የተወሰኑ የገበያ እድሎች ላይ የሚደረጉ የሁለትዮሽ ሲሆኑ ሌሎች ስምምነቶች ደግሞ በበርካታ መንግስታት በአህጉር ደረጃ የሚደረጉ እንደ የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ስምምነት (AfCAFTA) የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህ ሁለት ስምምነቶች የሚያስፈልጋቸው የክትትልና ግምገማ ይዘት ይለያያል። ለመጀመሪያው ስምምነት ጥቅል አመላካቾች እና መለኪያዎችን መጠቀም በቂ ነው።

የንግድ ስምምነቶች በበርካታ የኢኮኖሚ ክፍሎች ላይ የሚከናወኑ ሲሆኑ በንግዱ፣ በሸማቹ እና በሰራተኞች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽእኖ ለመቀነስ ሲባል ሰፊ ጊዜ የሚወስዱም ናቸው። ስለዚህ ክትትሉና ግምገማው ቅድሚያ ትኩረት ሊያደርግበት የሚገባው አንደኛ የፖሊሲዎቹን ተጽእኖ መቼ ማጥናት እንደሚያስፈልግ ሁለተኛው በተለያዩ የጊዜ አድማሶች ምን አይነት ጥያቄዎችና ዘዴዎች ያስፈልጋሉ እና በመጨረሻም ተጽእኖን ለማጥናት ምን አይነት ስልቶች ያስፈልጋሉ የሚሉት ወሳኝ ናቸው።

የንግድ ፖሊሲ ተጽእኖን ለማጥናት በሶስት የጊዜ አድማሶች በአጭር ፣ በመካከለኛ እና ረጅም ጊዜ በመወሰን ክትትልና ግምገማው ማከናወን ያስፈልጋል። የንግድ ፖሊሲን ለማሻሻል በሚደረገው ግምገማ እና ፍተሻ ገላጭ የሆኑየ ጥናት ዘዴዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፡ በጊዜ ሂደት የበለጡ መረጃዎች የሚገኙ ሲሆን በመካከለኛና ረጅም ጊዜ ጥናት ላይ መደበኛና ኢኮኖሜትሪክስ ትንተና ዘዴዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

በተጨማሪም የፖሊሲው አላማዎች ተፈጻሚ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለካት የሚያስችሉ የመለኪያ ዘዴዎች ያስፈልጋሉ። ፖሊሲው ያመጣውን ተጽእኖ ለመለካት የወጪ እና ገቢ ንግድ አመላካቾች ብቻ በቂ ስለማይሆኑ ሌሎች ተጨማሪ

የኢኮኖሚያዊ ውጤቶች (ለምሳሌ ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትምንት FDI) ፣ ማህበራዊ ግምገማዎች (ለምሳሌ የሥራ እድል፣ ደመወዝ እና የነፍስ ወከፍ ገቢ)፣ የከባቢያዊ ግምገማዎች (ለምሳሌ የበካይ ጋዞች መለቀቅ፣ የአየር ብክለት፣ ብዝሃ ህይወት፣ የውሀ ሀብትና ጥራት)፣ በሰውና በመሰረታዊ የሰራተኛ መብት ጥናት ላይ የተመረኮዙ ሊሆኑ ይችላሉ።

የንግድ ፖሊሲው ያመጣውን ተጽዕኖ ለመገምገምና ለማጥናት የተለያዩ አይነት አቀራረቦችን መጠቀም አስፈላጊ ነው። አሁናዊ የንግድ ስምምነቶች ተፈጻሚ የሆኑ ታሪፎችን በመቀነስ ብቻ ሳይወሰኑ በርካታ የኢኮኖሚ ዘርፎችን በማካተት እስከ 10 ዓመት እድሜ ሊራዘሙ የሚችሉ ይሆናል። በዚህ ጊዜ ውስጥ በርካታ የሀገር ውስጥ እና አለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊና ኢኮኖሚያዊ ያልሆኑ ምክንያቶች ንግድና ኢንቨስትመንቱ ላይ ተጽእኖ ሊያስከትሉ ይችላሉ። የንግድ ስምምነቶችና ፖሊሲዎች ተጽእኖ በውጤት በሚለካበት ጊዜ ግልጽ የሆነ መለያና መተንበያ ዘዴዎች ሊኖሩ ይገባል። ስለዚህ ወጥ የሆነ የአመልካቾች መረጃ አያያዝ ዘዴ፣ አቀራረብ የንግድ ፖሊሲው እርምጃዎችና የተገለጹ አላማቸውን ማሳካታቸውን እና አለማሳካታቸውን የሚለካበት ገላጭ ስታቲስቲካል ሞዴሎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ስለሆነም ሶስት ዘዴዎችን ማለትም ገላጭና የተተነተኑ መረጃዎች፣ ኢኮኖሜትሪክስ ሞዴሊንግ እና የመጠን መለኪያ አቀራረብ ማለትም ቅኝትን፣ ቃለመጠይቆችን፣ የኬዝ ጥናቶች፣ ወርክሾፕና ምክክሮች በማካሄድ መረጃ ይሰበሰባል። ሁሉም አቀራረቦች አስፈላጊና በተለያየ ጊዜ አድማሶች ሊተገበሩ የሚችሉ ናቸው። እነዚህ ዘዴዎችን ለመምረጥ ዋና ዋና ምክንያቶቹ የሚሆኑት የጥያቄው፣ የመረጃው መገኘት እና የጥናቱና ግምገማው ወጪዎች ናቸው።

ገላጭ ስታትስቲክስ (Descriptive statistics) :- የንግድ ስምምነቶች እና የንግድ ፖሊሲዎች የሚሰጡትን ጥቅሞች በፍጥነት ለማግኘት የሚያስችሉ ፈጣን እና ቀላል የአቀራረብ ዘዴ ነው። ይህም ሂደት ቀላልና ከንግድ ስምምነት ጋር የተገናኘ የታሪፍ ለውጥ፣ ከባድና ቀላል የንግድ ጠገግ (ማርጂን)፣ የአጠቃቀም መጠን፣ የሽፋን መጠን እና በንግድ ድርሻ ላይ ያለ ለውጥ በፍጥነት የንግድ ፖሊሲውን ተጽእኖ ለመለየት የሚያስችል ዘዴ ነው። ብዙዎቹ ስታቲስቲክስ ሞዴሎች በቀላሉ በሚገኝ መረጃ ላይ ተመስርተው ሊሰሉ ይችላሉ። ለምሳሌ ተመራጭ አጠቃቀም (preference utilization) - አንዳንድ ድርጅቶች በስምምነቱ የተሰጠውን የታሪፍ ነጻ ንግድ፣ የታሪፍና ታሪፍ ነክ ያልሆኑ

መሰናክሎችን መቀነስ፣ የመንግስታት የንግድና ኢንቨስትመንት ፍሰት ወዘተ ድንጋጌዎች አለአግባብ ሊበዘብዙ ይችላሉ፡፡ አብዛኞቹ አመልካቾች ብዙ የዳታ አቅርቦት አያስፈልጋቸውም፡፡ በተጨማሪም በተናጠል በምርት ወይም በዘርፍ ደረጃ ሊሰላ ይችላል፡፡ ሆኖም ገላጭ ስታቲስቲክስ የንግድ ፖሊሲዎች ያላቸውን ተጽእኖ የሚያሳይ ቢሆንም በንግድ ፖሊሲው ላይ የተፈጠረውን ምክንያታዊ ዳራ አያመለክትም፡፡

ግራቪቲ ሞዴሊንግ (Gravity Modeling)፡- ግራቪቲ ማለት የወርክሆርስ ሞዴል ሲሆን ኢኮኖሚስቶች በመንግስታት መካከል የተደረጉ የንግድ ስምምነቶችንና ፖሊሲዎችን ድህረና ቅድመ ተጽእኖችን የሚያጠኑበት ዘዴ ነው፡፡ ዋነኛ ማዕከሉ በግራቪቲ ሞዴል የሚገለጸው በመንግስታት ማካከል የተደረጉ ንግድ ስምምነቶች በሀገራቱ የኢኮኖሚ፣ የንግድ መጠን እና በሁለቱ ሀገሮች መካከል ያሉ እውቀቶችን ከግምት ያስገባል፡፡ ከግራቪቲ ሞዴሊንግ በተጨማሪ በኢንቨስትመንት ፍሰት ላይ የንግድ ስምምነቶች ያመጡትን ተጽእኖዎች ለመገመት ያስችላል፡፡ ዘዴው በጣም ውጤታማ እና በንግድ ስምምነቱ የተከሰተውን ድህረ ተጽእኖ ወይም የንግድ ፖሊሲው በረጅም ጊዜ ሂደት ያስከተለውን ተጽእኖ ለማጥናት የሚያገለግል ቢሆንም የአጭር ጊዜ ተጽእኖውን ለመለየት አያስችልም፡፡ ግራቪቲ ሞዴል ድምር ችግሮችን እንዲሁም የሀገር ውስጥ ምርት መጠን (GDP) እና ሌሎች በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ ያልተተነተኑ መረጃዎችን ለመለካት ይችላል፡፡ በተጨማሪም ግራቪቲ ሞዴል የታሪፍ ለውጦችና ከታሪፍ ውጪ ያሉ መሰናክሎች ያስከተሉትን ተጽእኖ ለመገምገም የሚያስችል የግምገማ ስልት ነው፡፡

ኮምፒቴብለ ጅኔራለ ኢኩሊብረም (Computable General Equilibrium/Partial Equilibrium (CGE))፦ ይህ ሞዴል በአመዛኙ የሚጠቅመው የማንኛውም የንግድ ስምምነት ወይም የንግድ ፖሊሲ ለውጥ በተለያየ አይነት ልዩነት ያስከተሉትን ተጽእኖ ለማጥናት ጥቅም ላይ የሚውል የሞዴል አይነት ነው፡፡ ሞዴሉ በአብዛኛው የንግድ ፖሊሲው ከመለወጡ በፊት የአንድ ዓመት መረጃ እና የፕሮጀክት ጥቅሞችን የሚለይ ነው፡፡ ሆኖም የንግድ ፖሊሲ ለውጦች ከተከናወኑ በኋላ ያለውን ድህረ ተጽእኖ ይለያል፡፡ ኮምፒዩቴብል ጀነራል ኢኩሊብሪየም ጥቅሙ በኢኮኖሚው ዘርፎች ውስጥ ያለውን ግንኙነት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው፡፡

ዲፈረንስ ኢን ዲፈረንሰ (Differences-in-differences)፦ የነጻ ንግድ ስምምነት በንግድ ፍሰቱ ላይ እንዲሁም በፍላጎት ላይ ያስከተለውን ምክንያታዊ ተጽእኖ ለማጥናት

የሚያገለግል የጥናት አቀራረብ ዘዴ ነው። የሚከናወነውም የፖሊሲ ለውጡን ተግባራዊ ባደረጉ እና ባላደረጉ አካላት መካከል ያለውን ለውጥ በማነጻጸር የሚተነትን ነው።

ኪሊቴቲቭ አፕሮች (Qualitative approaches)፦ የኪሊቴቲቭ አፕሮች ቅኝቶችን፣ የብዛት ቃለ መጠይቆችን፣ ኬዝ ጥናቶችን፣ ወርክሾፖች እና ምክክሮችን ያካትታል። እነዚህ የኪሊቴቲቭ አፕሮቾች የንግድ ፖሊሲዎችና ስምምነቶች በተመለከተ ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖር እንዲሁም ስለ ፖሊሲዎች ተጽእኖ ጥንካሬ ይፋ የሆነ ኪሊቴቲቭ ትንታኔ ለማድረግ ያስችላል። ይህ የአቀራረብ ስልት ቀደም ሲል በአግባቡ ያልተከናወኑ ኪሊቴቲቭ መረጃዎችን እና ውጤቶችን ለማሳየት አያስችልም። በተመሳሳይ ሁኔታ ድርድሮች ከመጀመራቸው በፊት የህዝብ ምክክሮችና ወርክሾፖች መንግስት መያዝ ስለሚገባው አቋም የሚገልጹ ጠቃሚ መረጃዎችን ያቀርባል። ኪሊቴቲቭ ስልት በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት። የመጀመሪያው ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ሊከናወን በመቻሉ ነው። ሁለተኛው በመደበኛ የኢኮኖሜትሪክ ሞዴሊንግ ሊመለሱ የማይችሉ ውስብስብ ጥያቄዎችን ለማሳየት በመቻሉ ነው። ሶስተኛው የንግድ ፖሊሲው ወይም የንግድ ስምምነቱ በተጀመረ አጭር ጊዜ ውስጥ ሊከወን መቻሉ ነው።

8.4.2 መረጃ መሰብሰብና መተንተን

አስተማማኝ፣ ወቅቱን የጠበቀ እና ጥቅል የሆነ የኢኮኖሚ መረጃዎችን መሰብሰብ የንግድ ፖሊሲዎችን ለመገምገም ለመከታተል እና ለመከለስ በጣም ወሳኝ ነው። ዝርዝር የሆነ የድርጅት ደረጃ መረጃ ከማዕከላዊ እስታቲክስ አገልግሎት፣ከጉምሩክ ኮሚሽን እና ገቢዎች ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የሚሰበሰብ ይሆናል።

9 ተያያዥ ፖሊሲዎች

የንግድ ፖሊሲ ከሚከተሉት ብሔራዊና የዘርፍ ፖሊሲዎች ጋር የተገናኘ ነው። ከእነዚህም መሀል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡

- የኢትዮጵያ ጥራት ፖሊሲ
- የግብርና እና የገጠር ልማት ፖሊሲ
- የኢንዱስትሪ ፖሊሲ
- የማዕድን ፖሊሲ

- የኢንተርፕራይዝ ፖሊሲ
- የቱሪዝም ፖሊሲ
- የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ

10 የፖሊሲው ስርጭት

የፀደቀው የፖሊሲ ሰነድ በህትመት፣በአይልይክትሮኒክ እና በሌሎች መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ይደረጋል።

11 ፖሊሲው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ፖሊሲው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ከፀደቀበት ከ-------ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

12 የቃላት ፍች

- የመቀበል አቅም፦ የአንድ ድርጅት አዳዲስ እውቀት አስፍላጊነትን የመለየት፣ የማዋሃድ እና የንግድ ስራ ለማድረግ መቻል ነው።
- የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና (AfCFTA)፡ በመላው አፍሪካ ወደ 1.3 ቢሊየን ለሚጠጉ ሰዎች የሸቀጦች እና አገልግሎቶች አንድ ገበያ በመፍጠር እና የአፍሪካን ኢኮኖሚያዊ ውህደት በማጠናከር በዓለም ትልቁን የነፃ ንግድ ቀጣና ለመመስረት ትልቅ ፍላጎት ያለው የንግድ ስምምነት ነው።
- የሁለትዮሽ እና የባለብዙ ወገን የንግድ ስምምነቶች፡- በሁለት ወገኖች እና ከሁለት በላይ በሆኑ ወገኖች መካከል ስምምነትን የሚያካትት የንግድ ስምምነት ነው።
- የውድድር ጥቅሞች፡- አንድ አገር ወይም ኩባንያ ከተወዳዳሪዎቹ በተሻለ ወይም በርካሽ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን እንዲያመርት የሚፈቅዱ ነገሮችን ያካትታል።
- ተወዳዳሪነት፡- ከሌሎች ኩባንያዎች፣ አገሮች፣ ድርጅቶች ጋር በተሳካ ሁኔታ መወዳደር የመቻል እውነታ ነው።
- ዲጂታል ንግድ፡- በኤሌክትሮኒክስ መንገድ በቴሌኮሙዩኒኬሽን እና/ወይም በአይሲቲ አገልግሎት የነቃ ንግድን የሚያመለክት ሲሆን በሁለቱም እቃዎችና አገልግሎቶች ንግድን ይሸፍናል።
- የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት፡- ከውጪ ሀገራት ይልቅ በአንድ ሰው ኩባንያዎች እና ምርቶች ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ።
- የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት (FDI)፡- ድንበር ተሻጋሪ የኢንቨስትመንት ምድብ ሲሆን በአንድ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለ ባለሀብት ዘላቂ ፍላጎት ያለው እና በሌላ ኢኮኖሚ ውስጥ ባለው የድርጅት ነዋሪ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድርበት ነው።
- በአለምአቀፍ እሴት ሰንሰለት (GVC) መሳተፍ፦ የብዙ ምርቶች ዲዛይን፣ ማምረት እና ግብይት አሁን በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ ኢንተርፕራይዞች መካከል የተከፋፈሉ የእንቅስቃሴዎች ሰንሰለት ያካትታል።
- የመንግስት እና የግል አጋርነት (PPP)፡- በመንግስት እና በግሉ ሴክተር ተቋማት መካከል የረጅም ጊዜ ዝግጅት ነው።

- አህጉራዊ ውህደት፡- ሰላም፣ መረጋጋትና ሀብትን ለማስፈን ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ብሔር ብሔረሰቦች ተባብረው ተቀራርበው ለመሥራት የተስማሙበት ሂደት ነው።

- የንፅህና እና የዕፅዋት ጤና ጥበቃ (SPS) ፡- እርምጃዎች የሰውን፣ የእንስሳትን ወይም የእፅዋትን ህይወትን ወይም ጤናን ከተባይ እና ከበሽታዎች መግቢያ፣ መመስረት እና መስፋፋት እንዲሁም ተጨማሪዎች ፣ መርዛማዎች እና አደጋዎች ከሚመጡ አደጋዎች ለመጠበቅ የሚተገበሩ የኳራንቲን እና የባዮሴኪዩሪቲ እርምጃዎች ናቸው።

- የታሪፍ እና የታሪፍ ያልሆኑ እንቅፋቶች፡- የታሪፍ እገዳዎች በመንግስት ታክስ ወይም ቀረጥ የሚጣሉት ከውጭ በሚያስገቡት ምርቶች ላይ ነው። ከታሪፍ ውጪ የሆኑ እገዳዎች መንግስት ከውጭ በሚያስገቡት ምርቶች ላይ ከጣለው ታክስ በስተቀር ሁሉንም ገደቦች ይሸፍናል።

- ለንግድ ቴክኒካል መሰናክሎች (ቲቢቲ)፡- የግዴታ ቴክኒካል ደንቦችን እና አንድ ምርት ሊኖረው የሚገባውን ልዩ ባህሪያት የሚገልጹ እንደ መጠኑ፣ ቅርፅ፣ ዲዛይን፣ መለያ ማድረጊያ/ማሸግ/ማሸጊያ፣ ተግባራዊነት ወይም አፈጻጸምን የሚገልጹ የፍቃደኝነት ደረጃዎችን ያመለክታል።

- ንግድ፦ በጅምላም ሆነ በችርቻሮ፣ በአገር ውስጥ ወይም በአገሮች መካከል ሸቀጦችን የመግዛት፣ የመሸጥ ወይም የመለዋወጥ ተግባር ወይም ሂደት ነው።

- የንግድ ነፃነት፡- በአገሮች መካከል የሚደረጉ የነፃ የሸቀጥ ልውውጥ ገደቦችን ማስወገድ ወይም መቀነስ ነው። እነዚህ መሰናክሎች ታሪፎችን፣ እንደ ግዴታዎች እና ተጨማሪ ክፍያዎች፣ እና ታሪፍ ያልሆኑ እንቅፋቶችን፣ እንደ የፍቃድ አሰጣጥ ደንቦች እና ኮታዎች ያካትታሉ።